# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ

## የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ

ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- ✓ የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- ✓ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- ✓ የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- ✓ የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- ✓ የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- ✓ የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

1. በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ክፍል አስር አንቀጽ 88/2 ቀጣሪው ተቀጣሪው ከአንድ በላይ የሆነ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እንዳለው ያወቀና ሌላው ቀጣሪ ወይም ሌሎች ቀጣሪዎች በጠቅላላው የተቀጣሪው ገቢ ላይ ተመስርተው የገቢ ግብሩን ቀንሰው እንደማያስቀሩ ያወቀ እንደሆነ ቀጣሪው የተቀጣሪውን ገቢ በማጠቃለል የግቢ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ እንዳለበት የተደነገገ ቢሆንም፣ **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** በድምሩ ብር 86,445.71፣ **በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ** ከመደበኛ በጀት ብር 422,345.88 እንዲሁም ከውስጥ ገቢ ብር **29,726.40**፣ **በሪፈራል ሆስፒታል ብር 51,654.68**፣ **በአጠቃላይ** ለተለያዩ ጉዳዮች ለስራ የመጡ እንግዳ መምህራን ካገኙት ክፍያ ወይም ገቢ ላይ የገቢ ግብር መቀነስ ሲገባው ቅድመ ታክስ 2 % (ሁለት በመቶ) በመቀነሱ በልዩነት (በብልጫ) በድምሩ ብር **590,172.67** ለመምህራኖቹ የተከፈለ መሆኑ፣
2. በበጀት ዓመቱ ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ገቢ በድምሩ ብር 73,019,883.12 እና ወጪ በድምሩ ብር 65,291,936.13፣ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ከፕሮጀክት ሂሳብ የተሰበሰበ ገቢ ብር 41,550,955.24 እና ወጪ ብር 53,096,883.13 የሂሳብ ሪፖርቱ ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያልቀረበ መሆኑ፣
3. በአጠቃላይ ድምር **ብር** 405,692.31 ክፍያዎቹ በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር የተከፈለ መሆኑ፣

4. በድምሩ **ብር** 18,320.00 ከርቀት ትምህርት መርሀ ግብር ገቢን ለማመንጨት የሚወጣው ወጪ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ቦርድ መወሰን ሲገባው በኮሌጁ ስራ አመራር ውሳኔ መሰረት **ከውስጥ ገቢ** የተከፈለ መሆኑ፣
5. ለትምህርት ወይም ሥልጠና በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር ተልከው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሠራተኞች ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ጊዜ የሚሄዱ ከሆነ ከተፈላጊ መረጃዎች ጋር ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ሲፈቀድ በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው እንደሚከፈላቸው የተገለጸ ቢሆንም፣
   - **በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** በድምሩ **ብር** 425,529.00 (91,385.00 + 334,144.00) ደመወዝ፣ አኑዋላይዜሽን፣ የትራንስፖርት አበል፣ የቤት አበል እና የሃላፊነት አበል ከመመሪያ ውጭ አላግባብ መከፈሉ፣
6. በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የቤት አበል ለማይገባቸው ለቴክኒካል አሲስታንስ I፣ II እና III በመመሪያው ከተፈቀደው ውጭ ብር 250.00 እና 239.81 ተመን በመፍቀድ በድምሩ ብር 281,046.31 የቤት አበል፣ የተከፈለ መሆኑ፣
7. ከዩኒቨርሲቲው ለኦዲት ተጠይቆ በቀረበው የህንድ መምህራን መረጃ መሰረት ከሁለት ዓመት በላይ ለሆናቸው የወር ደመወዝ ሲከፈል የስራ ግብር መቀነስ ሲገባው በበጀት ዓመቱ ብር 5,193,350.12 መቀነስ እና ለሚመለከተው መ/ቤት ገቢ መሆን የነበረበት የስራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፣
8. ግዢዎች በመመሪያው መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣
   - **በዋናው ግቢ** በድምሩ የብር 16,954,994.98 የተለያዩ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ጥንድ አልጋ፣ ሎከር፣ ቴብል ቼር፣ ጠረጴዛ እና የብር 4,565,958.00 ስጋ፣ በድምሩ የብር 21,520,952.98 ግዥ፣
   - **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** በድምሩ የብር 1,495,920.00 የስጋ ግዥ፣
   - **በግብርና ኮሌጅ** የብር 727,280.00 **የስጋ ግዥ፣**

   በአጠቃላይ ድምር የብር 23,744,152.98 የስጋ እንዲሁም የተለያዩ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ጥንድ አልጋ፣ ሎከር፣ ቴብል ቼር፣ ጠረጴዛ ከዩኒቨርሲቲው ኢንተርፕራይዝ ያለውድድር ግዥው በቀጥታ የተፈጸመ መሆኑ፣
9. **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት**፣
   - ለኬሚካል፣ ለሲቪል ኢንጅነሪንግ፣ ለኤሌክትሪካል እና ለሜካኒካል ት/ክፍሎች የሚያገለግሉ በአንድነት በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም የሚገባቸው በድምሩ

**የብር 5,314,995.80** የላቦራቶሪ ዕቃዎች ተከፋፍለው በዋጋ ማቅረቢያ የተገዙ መሆኑ፣ በተጨማሪም፣

- ተቋሙ በተደጋጋሚ በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በግዥ ሥራ ክፍሉ የገበያ ጥናት የማይደረግ እና በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ከሚወጣው ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኋላ ግዥው እየተፈጸመ አለመሆኑ፣
- እቃዎች በተፈላጊ ባህርያት ዝርዝር /Specification/ ለመቅረባቸው ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ወይም የጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ የጽሑፍ ማረጋገጫ ሳይቀርብ እቃዎቹ ገቢ የሆኑ እና ክፍያው የተፈጸመ መሆኑ፣በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

10. **በአጠቃላይ በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለ2008** በጀት ዓመት ለተፈጸመ ግዥ የሰራተኞች ደንብ ልብስ እና የላብራቶሪ እቃዎች ግዥ በበጀት እጥረት ምክንያት ሳይከፈል የቀረ በማለት በ2009 በጀት ዓመት በድምሩ **ብር 626,778.86** ተከፍሎ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
11. እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ ብር **6,128,335.34** (ብር**3,282,177.33** የመደበኛ በጀት እና ብር **2,846,158.01** የውስጥ ገቢ) ተሰብሳቢ ሂሳብ እና ብር 9,474,830.81 ተከፋይ ሂሳብ (ብር 2,655,164.19 የመደበኛ በጀት እና ብር 6,819,666.62 ብር የውስጥ ገቢ) ያልተወራረደ መሆኑ፣ በተጨመሪም በውዝፍ ከሚታይ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በሂሳብ አርዕስት 5054 ለተያዘ ብር **87,000.00** በተከፋይ ሂሳብ ለመያዝ የሚያስችል ማስረጃ የሌለው መሆኑ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሣብ መግለጫዎች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፣ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

<u>ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)</u>

- **በዋናው ግቢ** በድምሩ ብር 2,998,053.14 እና **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** በድምሩ ብር 397,158.50፣ በአጠቃላይ ድምር **ብር 3,395,211.64** ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር ፈቃድ ሳይገኝ በኮንትራት/በጊዜያዊ ለተቀጠሩ ሠራተኞች የተከፈለ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በተጨማሪም ለቦታው የሚያስፈልገው የሰው ሃይል

በጥናት ባልተደረሰበት ሁኔታ ከፍተኛ የሰው ሃይል በመጠቀም ክፍያው ወጪ ቆጣቢ አሰራርን እና መመሪያን ያልተከተለ መሆኑ፣

- **በሪፈራል ሆስፒታል** በድምሩ **ብር** 185,109.75 ለጤና ባለሙያዎች የተረኝነት አበል ክፍያ ሲከፈል ወሩን ሙሉ ቀንም ማታም የጤና ባለሙያዎቹ ስራ ገብተው ስለመስራታቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ሰነድ ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ከ10% በላይ ብር 12,000,613.49 ያልተሰራበት በጀት መኖሩ፣

**<u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>**

1. **<u>ንብረት (አላቂ እና ቋሚ እቃዎች)</u>**

**<u>ዋናው ግቢ፣</u>**

**የአላቂ እቃ ንብረት ክፍል**

- ብዛቱ 5,612 እሽግ የሚሆን አዳዲስ ለማስተማሪያነት የተገዙ ጠመኔዎች ከሁለት ዓመት በላይ ያለጥቅም በንብረቱ ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፤

**የምግብ ቤት ንብረት ክፍል**

- በጁኒየር ተማሪዎች መመገቢያ ሚኒ ስቶር ውስጥ የምግብ ጥሬ እቃዎች ማለትም ጥቅል ጎመን፤ ድንች፤ ሽንኩርት፤ ካሮት የመሳሰሉት አትክልቶች ለአቀማመጥ ምቹ ባልሆነ ወይም ከመሬት ከፍታ በሌለው ሁኔታ መሬት ላይ የተቀመጡ መሆኑ፣

**የተመላሽ ንብረት ክፍል**

- በተመላሽ ንብረት ክፍል ውስጥ በ2005 በጀት ዓመት ተመላሽ የሆኑ ብዛት 35 ዴል ኮምፒውተር፣ በ2006 በጀት ዓመት ተመላሽ የሆኑ ብዛት 84 ኤች ፒ ኮምፒውተር፣ ብዛት 179 አሰር ኮምፒውተር እንዲሁም ብዛት 162 ዴል ኮምፒውተር ተጠግነው አግልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ በባለሙያ ሳይረጋገጡ ወይም ሳይለዩ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣

**የመድሃኒት አያያዝ**

- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች/የተበላሹ መድኃኒቶች/ 109 አይነት የተለዩ መድሃኒቶች ከ2002-2008 በጀት ዓመት ጀምሮ በተለያየ ጊዜ የገቡ መድሃኒቶች በአንድ መጋዘን ውሰጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

- ከዋናው የመድኃኒት ስቶር የወጣው መድኃኒት እና በፕሪስክሪፕሽን ወረቀት ላይ የተመዘገበው መድኃኒት ከወጪ ቀሪ መከታተያ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ ተገናዝቦ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣
- በቴክኖሎጂ ኢንስቲተዩት ተማሪዎች ምግብ አዳራሽ ተጠናቆ ርክክብ ተፈጽሞ የካቲት /2009 ዓ.ም ስራ መጀመሩ በክፍሉ ሰራተኞች የተገለጸ ቢሆንም የክፍሉ ጣሪያው የሚያፈስ እና ኮርኒሱ ያልተስተካከለ መሆኑ፣

2. <u>ልዩልዩ</u>

- ዩኒቨርሲቲው የየወሩ የተጣራ የሰራተኞች ደመወዝ በባንክ በኩል በሚከፈልበት ወቅት የሰራተኞች ስም፤ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እና የወሩ የተጣራ የደመወዝ መጠን የያዘ ዝርዝር በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ ክፍያ ወደሚፈፅመው ባንክ መተላለፍና ክፍያውም ከተፈፀመ በኋላ ባንኩ የሰራተኞቹን ስም ዝርዝር የያዘውን ሰነድ ላይ በሚመለከተው ኃላፊ ተፈርሞና ክብ ማህተም ተደርጎበት አንድ ኮፒ መልሶ ለተቋሙ መላክ ሲገባው፤ ከባንኩ ማረጋጋጫ ሳይቀርብ በቀጥታ በባንክ ዴቢትና ክሬዲት አድቫይስ ብቻ የተጣራ የሰራተኞች ደመወዝ ክፍያ የሂሳብ ምዝገባ የተከናወነ መሆኑ፣

3. <u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች፣</u>

- በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2(በ) መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በውጭ ኦዲት ወይም በውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተመለከተው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡
- በተጨማሪም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰርት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና እርምጃ ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ፣

**<u>የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት፣</u>**

- የዩኒቨርሲቲው መምህር ለሆኑት አንድ ፕሮፌሰር የሁለት ምሁራንን የምርምር ሥራ ለገመገሙበት ብር 3,000.00 ክፍያ ሲፈፀም የተቆረጠው ብር 1,615.39፤ እንዲሁም ከሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የኤም.ፒ.ኤች ተማሪዎችን ላማከሩና ለፈተኑ መምህራን ከተፈፀመው ጠቅላላ ክፍያ ብር 47,600.00 ላይ የተቀነሰው ስራ ግብር ብር 15,960.00፤ በድምሩ ብር 17,575.39 የስራ ግብር ከተጠቃሚዎቹ መቀነስ ሲገባው አለአግባብ ከውስጥ ገቢ በመሸፈን ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤
- **በዋናው ግቢ በህክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ ከሪፈራል ሆስፒታል በአዋዳ ቢዝነስ ኮሌጅ** በተመረጡ ናሙናዎች ለተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ለፋሲሊቲ ሠራተኞች፤ ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ፤ ለዲሲፒሊን ኮሚቴ አባላት፤ ለተማሪዎች ዲሲፒሊን ኮሚቴ አባላት፤ ለፒፒኤም ኮሚቴ አባላት፤ ለሆስፒታል ማናጀርና ለፕላን ኤክስፐርት፤ ለMPH ሠራተኞች፤ ለቢፒአር ካሚቴ ለሥልጠና ማዕከል አስተባባሪ በሚል ለፕሮፎርማ ከፋች፣ ለረዳት ሪጅስራሮች እና ለዳታ አናሊስቶች የማበረታቻ ክፍያ፤ በጠቅላላው ብር 1,689,890.96 ያላግባብ የተከፈለ መሆኑ፤

**<u>የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት፣</u>**

**የወጪ ሂሳብ፣**

ዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ካውንስል የተለያዩ ውሳኔዎችን በመስጠት ከተፈጸሙ ክፍያዎች ውስጥ፡-

- ዩኒቨርስቲው በሥራ አመራሩ ውሳኔ የክረምት የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች ለመፈተን የመጡ መምህራን ለዋና አማካሪዎች (ለአድቫይዘር) በዋና ግቢ ብር **851,570.00**፣ በጤና ሳይንስ እና ሪፈራል ሆስፒታል ብር 84,000.00 ተከፍሎ መገኘቱ፣
- በዋና ግቢ ብር 508,091.00 ለመምህራን ከተከፈለው የትርፍ ሰዓት ክፍያ የሥራ ግብር መቀነስ ቢኖርበትም ዩኒቨርስቲው በራሱ ብር 169,941.00 ታክስ ሸፍኖ በአጠቃላይ ብር **1,105,511.00** ደንብና መመሪያ ሳይኖረው ከፍሎ መገኘቱ፡
- በአካዳሚክ የትምህርት ጥራት ለተሳተፉ በሚል በዋና ግቢ ብር 150,250.00፣ በቴክኖሎጂ ኮሌጅ ብር 133,566.00 እና በግብርና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 161,806.00፣ በድምሩ ብር 445,622.00 የማበረታቻ በሚል ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ዩኒቨርስቲው የኮሌጅ ኃላፊዎች ውስጥ ለሚገኙ የአስተዳደር ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ፈቃድ ሳይገኝ በጤና ሳይንስ እና ሪፈራል ሆስፒታል ብር

**53,601.75** እና በወንዶ ገነት ኮሌጅ ብር 15,300.00፣ በድምሩ ብር **68,901.75** የቤት አበል ተከፍሎ መገኘቱ፣

- ብር 5,329,915.35 በሥራ አመራር ካውንስል ውል ፈታኞችና የአማካሪዎች፣ የማበረታቻና የአስተባባሪነት፣ ለአስተዳደር ሠራተኞች የቤት አበል፣ ለስፔሻልስት ሀኪሞች እና ለጠቅላላ ሀኪሞች፣ ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ድጋፍ በሚል ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ መገኘቱ፣

**የውስጥ ገቢ ሂሳብ፣**

- የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ የአከፋፈል ሥርዓትን በተመለከተ በብልጫ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር **288,792.00** መኖሩ፣
- በሥራ አመራር ውሳኔ የዋና እና ረዳት አማካሪዎች፣ ለውስጥና ለውጭ ፈታኞች ማበረታቻ በሚል ብር **1,022,171.11** መከፈሉ፣
- ተገቢው የክፍያ ተመን/ሬት/ ዝርዝር ማስረጃ ሳይቀርብ የተከፈለ ብር **2,009,690.70** ሲሆን፣ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ከመምህራን ከሚከፈላቸው መቀነስ የነበረበት የሥራ ግብር ብር **237,596.85** በዩኒቨርስቲው ተሸፍኖ መገኘቱ፣

**ተሰብሳቢ ሂሳብ**

- በ4202 ሂሳብ መደብ በጥሬ ገንዘብ ጉድለት በአቶ መስፍን ደሴ ስም በተቀጽላ ሌጀር ቁጥር 10 ብር 38,380.94 ያልተሰበሰበና ምንም እቅስቃሴ ሳይደረግበት አሁንም በተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፡-

**<u>የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት፣</u>**

- በኃላፊነት ላይ ላሉ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ ለቴክኒክ አሲስታንት አለአግባብ የተከፈለ የቤት አበል እና ጥቅማ ጥቅም ብር 1,622,360.46 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- በክረምት ዲፕሎማ መረሀ ግብር ለተሳተፉ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች አላግባብ የተከፈለ ብር 1,089,675.30 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- ለሐዋሳ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ለዩኒቨርስቲው መኖሪያ ቤት የውል ቁጥር 416 የተከፈለው ብር 41,548.05 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣

- በመደበኛ የሥራ ሰዓት የንብረት ቆጠራ ያደረጉ፣ በተማሪዎች የምረቃ በዓል ያለአግባብ የውሎ አበል የተከፈለ ብር 188,343.00 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- ብር 203,978.08 ለዲስፒሊን ኮሚቴ፣ ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ፣ የጥራት እና የቁጥጥር ኮሚቴ እና ሌሎች በሥራ አመራር ውሳኔ የተከፈለ ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- ከወንዶ ገነት የተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ሲከፈል መቀነስ ያለበት ታክስ ብር 132,700.00 በኮሌጅ የተሸፈነው ሂሳብ ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- በአስተዳደር ሠራተኞች ላሉ የተለያዩ ክፍሎች ያለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 101,867.05 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- የኢፌድሪ ት/ት ሚኒስቴር ካወጣ የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ውጭ ተከፍሎ የተገኘ ብር 374,860.00 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- ብር 5,116,841.79 ከተለያዩ ድርጅቶች መሰብሰብ ያለበት ቅጣት ወደ ገ/ኢ/ል/ሚ ፈሰስ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣

በሚሉ ግኝቶች ላይ እስከ 2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማብቂያ ጊዜ ድረስ እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፣

**ከማክበር ሰላምታ ጋር**

**የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

# የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

**መግቢያ፣**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም ድጋሚ በወጣው የማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

**ዓላማ፣**

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት ፣**

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን ፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በሀዋሳ

ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የገቢ ሂሳብ</u>፣

1.1 <u>ከተገኘው ጥቅም ላይ ያልተቀነስ ስራ ግብር፣</u>

1.1.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ክፍል አስር አንቀጽ 88/2 ቀጣሪው ተቀጣሪው ከአንድ በላይ የሆነ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እንዳለው ያወቀና ሌላው ቀጣሪ ወይም ሌሎች ቀጣሪዎች በጠቅላላው የተቀጣሪው ገቢ ላይ ተመስርተው የገቢ ግብሩን ቀንሰው እንደማያስቀሩ ያወቀ እንደሆነ ቀጣሪው የተቀጣሪውን ገቢ በማጠቃለል የገቢ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ይሁን እንጂ፣

- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** በድምሩ ብር 86,445.71፣ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 1 ተይዟል)
- **በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ** ከመደበኛ በጀት ብር 422,345.88 እንዲሁም ከውስጥ ገቢ ብር 29,726.40፣ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 2 ተይዟል)
- **በሪፈራል ሆስፒታል ብር 51,654.68**፣ (ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 3 ቀርቧል፡፡)

**በአጠቃላይ** ለተለያዩ ጉዳይ ለስራ የሚመጡ እንግዳ መምህራን ካገኙት ክፍያ ወይም ገቢ ላይ የገቢ ግብር መቀነስ ሲገባው ቅድመ ታክስ 2 % (ሁለት በመቶ) በመቀነሱ በልዩነት (በብልጫ) በድምሩ ብር **590,172.67** የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

1.1.2 <u>ስጋት፣</u>

መንግስት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ወይም ገቢ ሊያጣ ይችላል፡፡

1.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

በአንድ አገልግሎት ውል ከብር ሶስት ሺህ በላይ የሚፈጸም ክፍያ በንግድ ስራ ብቻ ለተሰማሩ ግብር ከፋዮች ከጠቅላላ ክፍያው ላይ 2% (ሁለት በመቶ) ተቋሙ ግብር

ቀንሶ ማስቀረት እንዳለበት አዋጁ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ግን በንግድ ሥራ ዘርፍ ላልተሰማራ ተቀጣሪው በሌላ ድርጅት ወይም ተቋም ተቀጥሮ መሥራቱ የሚታወቀው ከሆነ የተቀጣሪውን ገቢ በማጠቃለል ተቋሙ የገቢ ግብር ቀንሶ ማስቀረት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ከተቋሙ ውጭ ሆነው ከክፍያው ላይ 2 % (ሁለት በመቶ) የሚቀነስባቸው ተቀጣሪዎች በንግድ ስራ ዘርፍ የተሰማሩና ለንግድ ስራ ብቻ ተብሎ የሚሰጠውን የግብር ከፋይ መለያ የሚያቀርቡ መሆን አለባቸው፡፡

በመሆኑም በልዩነት በብልጫ የተከፈለው ታክስ ከሚመለከተው አካል ተመላሽ ሊሆን ይገባል፡፡

1.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣፣</u>

**የሥራ አመራሩ፣**

- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** በአሁኑ ወቅት ያለው የተማሪ ቁጥር ከ12,000.00 /አስራ ሁለት ሺህ/ በላይ ሲሆን እነዚህ ተማሪዎች በየሴምስተሩ ፈተና በሚፈተኑበት ጊዜ ለትምህርት ጥራት የአንድ ክፍል ተማሪዎችን ከ3 እና 4 በላይ ክፍሎች ተደልድለው ፈተና ሲሰጥ የመምህሩ ቁጥር ውስን በመሆኑ ከተቋሙ ውጭ እንግዳ መምህራን ተጋብዘው እንዲፈትኑ ሲደረግ የፈታኞች ክፍያ Tin number በማያያዝ ለክፍያ ሲቀርብ ቅድመ ታክስ ተቀንሶ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ሲደረግ መቆየቱን፣ ሆኖም ግን ከነሐሴ 8/2009 ዓ.ም በቁጥር 20/111/2536/171/20 በተፃፈ ደብዳቤ በተላለፈልን ግልጽ መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ያደረግን ሲሆን ለአብነት 2010 ዓ.ም የመጀመሪያ ሴሚስተር የፈታኞች ክፍያ ሲፈፀም በአግባብ ግብር ቀንሰው የሠሩ መሆኑን፣
- **በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ** ከኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቁጥር 20.111/2536/171/20 በቀን ነሐሴ 8/2009 ዓ/ም ለኮሌጁ በተጻፈ ደብዳቤ በአንድ እቃ አቅርቦ ዉል ከብር አስር ሺህ /10,000.00/ በላይ እንዲሁም በአንድ አገልግሎት ዉል ከብር ሶስት ሺህ /3,000.00/ በላይ የሚፈጸም ከሆነ ከከፍያዉ ላይ ሻጩ ወይንም አቅራቢዉ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲሁም የንግድ ስራ ፈቃድ እንዳለዉ ሲረጋገጥ 2 ፐርሰንት የሚቀነስ ሲሆን፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሆነ እንዲሁም የንግድ ስራ ፈቃድ የሌለዉ ከሆነ ከክፍያዉ ላይ 30 ፐርሰንት መቀነስ እንዳለባቸው በደብዳቤዉ ላይ በገለጸላቸው መሰረት ከደብዳቤዉ በኋላ በቀጥታ 30 ፐርሰንት እየቆረጡ እንደሚገኙ፣ ሆኖም መመሪያዉ የደረሳቸው

የ2009 በጀት አመት ካለቀ በሁዋላ በመሆኑ ይህ ችግር ሊፈጠር መቻሉን፣ገልጸዋል፡፡

1.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>፣

ግኝቱን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተጻፈ መመሪያ ለዩኒቨርሲቲው የደረሰው በነሀሴ ወር 2009 መሆኑ በምላሹ የተጠቀሰ ቢሆንም ከሀምሌ 1/2008 ጀምሮ በተገኘ ገቢ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተጠቅሶ በወጣው የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 መሠረት የገቢ ግብሩ መቀነስ ሲገባ አለመቀነሱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም በግኝቱ ያለውና ቀደም ሲል ያልተቀነሰው ሂሳብ የሚፈለግባቸው ሰዎች በየአድራሻቸው ተፈልገውም ቢሆን ግብሩ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

1.2 <u>በመመሪያው በተቀመጠው የሪፖርት ይዘት መሰረት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ የውስጥ ገቢ እና የፕሮጀክት ሂሳብ</u>፣

1.2.1 <u>ግኝት</u>፣

- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ አንቀጽ 8/3 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተመረመረ የኦዲት ሪፖርት በደረሳቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሪፖርቱን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማቅረብ እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡
- በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 1 እና 2 ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ከውጭ አገር ለጋሽ መንግስታት የሚያገኘውን የብድርና የእርዳታ ገንዘብ ከሚኒስትሩ በቻናል አንድ የገንዘብ ፍሰት የተላለፈውን፣ በመ/ቤቱ ባንክ ቀጥታ ከአበዳሪና እርዳታ ሰጪዎች የገባውን ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ መሰረት የተዘጋጁትን ቻርት ኦፍ አካውንትስ፣ ቫውቸር፣ መዝገቦችና የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችን በመጠቀም ሂሳቡን መዝግቦ መያዝና ወርሃዊ፣ የሩብ አመትና ዓመታዊ ሪፖርት ከባንክ መግለጫው ጋር ማቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

  በዚህም መሰረት የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ እና የፕሮጀክት ሂሳብ ኦዲት ኦዲት ሲደረግ፣

- በበጀት ዓመቱ ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ገቢ በድምሩ ብር 73,019,883.12 እና ወጪ በድምሩ ብር 65,291,936.13፣ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ከፕሮጀክት ሂሳብ የተሰበሰበ ገቢ ብር 41,550,955.24 እና ወጪ ብር 53,096,883.13 የሂሳብ ሪፖርቱ ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያልቀረበ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ታውቋል።

1.2.2 <u>ስጋት</u>፣

- የሂሳብ ሪፖርቱ ለሚመለከተው መ/ቤት እንዲታወቅ አለመደረጉ በዩኒቨርሲቲው የፋይናንስ ግልፀኝነት እንዳይኖር እና የመንግስት ሃብት እንዳይታወቅ ሊያደርግ ይችላል።

1.2.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

- ዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢም ሆነ የፕሮጀክት ሂሳብ እንቅስቃሴን በመመሪያው መሰረት በወቅቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል።

1.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

የሥራ አመራሩ፣

- በሰኔ 2009 የመደበኛውን ሂሳብ ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባቀረቡበት ጊዜ አብሮ የውስጥ ገቢ ሪፖርት ያቀረቡ ቢሆንም "በበጀት ያልተደገፈ ሪፖርት አንቀበልም" ስለተባለ መመለሳቸውን፣ ነገር ግን አሁን በተሰጣቸው አስተያየት መሰረት ኦዲት የተደረገውን የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚያቀርቡ እና በቀጣይም የ2010 የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት በየወሩ ከመደበኛው ሂሳብ ሪፖርት ጋር ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚያቀርቡ፣
- **የፕሮጀክት ሂሳብን** በተመለከተም በዚሁ መሰረት የሪፖርት ሥርዓቱ ከተዘረጋ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያቀርቡ መሆኑን፣

በላኩት ምላሽ ገልጸዋል።

3. <u>የወጪ ሂሳብ</u>፣

3.1 <u>ደመወዝና ተዛማጅ ወጪዎች</u>፣

3.1.1 <u>የክፍያ ተመን ሳይኖረው የተፈፀመ ክፍያ</u>፣

3.1.1.1 <u>ግኝት</u>፣

በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ሌጂስሌሽን የአካዳሚክ ባለሙያዎች ግዴታዎች በሚለው ስር ተማሪዎችን ማማከር፣ ፈተና መፈተን፣ የማስተማሪያ መሳሪያ መከለስ እና

የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን እንዳለበት ተጠቅሷል። በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጥር 13/2003 በቁጥር ጠ80-አጠ52/02/13 በተጻፈ ደብዳቤ ከትምህርት ሚኒስቴር የቀረበለትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመምህራን የተሻሻለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በተፈቀደው አግባብ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር፡-

- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** ለማስትሬት ዲግሪ በሚዘጋጅ የጥናት ምርምር ጽሑፍ /Thesis Dissertation Research Defense/ ብር 2,000.00 እና ብር 3,500.00 ለረዳት እና ለዋና አማካሪዎች እንደቅድም ተከተላቸው እንዲሁም ለውስጥ ፈታኝ /Internal Examiner/ ብር 1,500.00፣ ለውጭ ፈታኝ /External Examiner/ ብር 2,000.00 እና ለሊቀመንበር /Chairperson/ ብር 500.00 በጥናት የምርምር ጽሑፍ ወረቀት ልክ በማድረግ የተፈቀደ ወይም የታወቀ የክፍያ ስርዓት በሌለበት ሁኔታ በቀን 30/03/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 790084 ብር 55,384.62፣ በቀን 30/06/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 790611 ብር 131,538.47፣ በቀን 16/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 794155 ብር 160,769.22፣ በድምሩ **ብር 347,692.31**
- **በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ** የ MPH & Ioso thesis deffence ለፈተኑ ለአንድ ተማሪ ብር 2,000.00 በማሰብ ለአምስት መምህራን ብር 58,000.00 በጠቅላላው የክፍያ ተመን ሳይኖረው ብር 405,692.31 ከመደበኛ በጀት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

3.1.1.2 **ስጋት፣**

በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ተጠያቂነት ያመጣል፡፡

3.1.1.3 **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር ክፍያ መፈጸም አግባብ ባለመሆኑ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ስለሚከፈለው የክፍያ ተመን ጥናት ተደርጎ በሚገኘው ውጤት መሰረት መስፈርት ወይም መመዘኛ

/Criteria/ ተዘጋጅቶ እንዲሁም የክፍያ ተመኑ ወይም መጠን በሚመለከተው መ/ቤት በማስፈቀድ ክፍያውን ሊፈፅም ይገባል፡

3.1.2.1 <u>ግኝት</u>፣

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 የውስጥ ገቢ መጠን እንዲሁም ገቢውን ለማመንጨት የሚወጣው ወጪ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ቦርድ እንደሚወሰን ይገልፃል፡፡

በዚሁ መሰረት የተቋሙ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ክፍያ ሲፈጸም በመንግሰት በወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- **በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ** በቀን 30/01/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 577886 ከርቀት ትምህርት መርሀ ግብር በተለያዩ የስራ ክፍል ኃላፊዎች የኃላፊነት ደረጃዎችን መሰረት ባደረገ መልኩ ለቺፍ ኤክስኪቲቪ ዳይሬክተር ብር 4,320.00፣ ለቺፍ አካደሚክና ምርምር ዳይሬክተር ብር 2,400.00፣ ለቺፍ ክሊኒካል ዳይሬክተር ብር 2,400.00፣ ለቼፍ አስ/ቢዝ/ልማት ዳይሬክተር ብር 2,400.00፣ ለሌሎች በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች ከብር 600.00 እስከ 800.00፣ በድምሩ **ብር 18,320.00** ከርቀት ትምህርት መርሀ ግብር ገቢን ለማመንጨት የሚወጣው ወጪ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ቦርድ መወሰን ሲገባው በኮሌጁ ስራ አመራር ውሳኔ መሰረት **ከውስጥ ገቢ** የተከፈለ መሆኑ፣

3.1.2.2 <u>ስጋት</u>፣

በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ሳይጸድቅ ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ተጠያቂነት ያመጣል፡፡

3.1.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፤

ዩኒቨርሲቲው ቀጣይነት ካላቸው የመማር ማስተማር ሂደት የሚገኙ ገቢዎችን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 በተቀመጠው አግባብ መሰረት በየደረጃው የሚወስኑ አካላቶችን በማስወሰን ክፍያ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

3.1.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

የሥራ አመራሩ፣

- **የዋናው ግቢ ምላሽ** በዩኒቨርሲቲው መምህራን ለሰሩበትና ክፍያ ለሚያስፈልጋቸው ሥራ ክፍያ የሚፈትሙት በLEH (Lecture equivalent hour) በተላከ ስሌት ሲሆን፣ መምህራኑም በአላቸው የአካዳሚክ ማዕረግ መሠረት የሚከፈለው የገንዘብ መጠን እንደሚወሰን እና በዚሁ መሠረት መምህራኑ ያስተማሩበትንና ያማከሩበትን

እንደዚሁም የድህረ ምረቃ ተመራቂ ተማሪዎችን የፈተኑበትን የሥራ ጫና ወደ LEH በመቀየርና እንደየአካዳሚክ ማዕረጋቸው በተቀመጠው "Rate" በማብዛት ክፍያዎቹ የተፈጸሙ መሆናቸውን፣

- **በሪፈራል ሆስፒታል፡-**

➢ የስጋት **ተጋላጭነት** ለነርሶች ለተፈቀደላቸው ክፍሎች በመደበኛ በመመሪያው መሰረት ብር 470.00 ከሚከፍላቸው ውጪ ከውስጥ ገቢ ብር 700.00 ተጨማሪ በመክፈል በየወሩ በድምሩ ብር **105,980.00** በአመራር ውሳኔ የተከፈለ ለተባለው በICU እና NICU የሰራተኞች የስራ ጫና ክፍያ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በተፈቀደው ብር 470.00 ወጪ ከውስጥ ገቢ ብር 700.00 ብር የክፍሎች የስራ ባህሪ የተነሳ የስራ ጫና ክፍያ በክፍሉ ለሚሰሩ ነርሶች **የሆስፒታሉ ቦርድ ቃለ- ጉባኤ ቁጥር HRH7098/08** በቀን 05/12/08 ዓ.ም በተጻፈው የውሳኔ ሀሳብ የተፈጸመ ክፍያ መሆኑን፣

➢ ከውስጥ ገቢ ክፍያ ተፈጽሟል ለተባለው **የሜዲካል ሰርተፊኬት** አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በተለያዩ ሆስፒታሎች በክፍያ የሚሰራ በመሆኑ እና ተመሳሳይ የክፍያ ጥያቄ በሀኪሞች እየተጠየቀ የሚገኝ እንደሆነ የተገለጸ በመሆኑ በሌሎች ሆስፒታሎች እየተከፈለ ያለውን የክፍያ መጠን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሆስፒታሉ ለአንድ ሰርተፍኬት ለሀኪሞች 100.00 ብር እና ለሆስፒታሉ ገቢ የሚደረግ 100.00 ብር **በማኔጅመንት እንዲከፈል በቁጥርHRH855/05 በቀን 24/11/05** በተወሰነው ውሳኔ መሰረት መከፈሉን፣

➢ **በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፡-**

- **ለ ኤም ፒ ኤች ቴሲስ ዲፌንስ ለፈተኑ** ለአንድ ተማሪ ብር 2,000.00 በማሰብ ለአምስት መምህራን ብር 58,000.00 ለተከፈለዉ ክፍያ ለማስተርስ እና ለስፔሻሊስት ፕሮግራሞች ለኤክስተርናል ኤግዛማይነርስ **በሴኔት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሴክ ቁጥር 08/2008** በነሐሴ 18/2008 ዉይይት ተደርጎ በተወሰነዉ መሰረት የተፈጸመ ክፍያ መሆኑን፣
- በፒቪ ቁጥር 577661 **ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴዎች የትርፍ ሰአት** ክፍያ ወደ አበል ተቀይሮ እንዲከፈላቸዉ በቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ተወስኖ ተከፍሎአል ለተባለዉ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴዎቹ ይህንን ሰነድ የማጽደቅ ስራ የሚያከናዉኑት ከኮሌጁ ዉጪ በመሄድ የሚያከናዉኑ በመሆኑ በአበል ክፍያዉ መከፈሉን፣
- **ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለተማሪዎች መማክርት አይ አር ቢ ኮሚቴዎች** እና ዳታ አናሊስቶች ቶፕ አፕ ለሚለው የዳታ አናሊስቶች ክፍያ የሚከፈለዉ የዳታ አናሊስቶች እጥረት ስላለ በመሆኑ በ |(Minute No CAC-005/08) በፀደቀዉ መሰረት እየተከፈለ እንደሚገኝ፣

- **በጤና ሳይንስ ኮሌጅ** በቀን 30/01/2009 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ 577886 በውስጥ ገቢ ሂሳብ ክርቀት ትምህርት መርሃ ግብር ለተለያዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ብር 18,320.00 የተከፈለው በዩኒቨርሲቲው ሥ/አ/ቦርድ በቁጥር ሀ/ዩ/ቦ-49/2009 ወውሳኔ መሆኑን፣

**ቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩት፡-**

- በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በተለያዩ ትምህርት ኘሮግራሞች 2ኛ ዲግሪ /Master program/ እንደሚሰጥ የሚታወቅ በመሆኑ ለውጭ ፈታኝ /External examiner/፣ ለውስጥ ፈታኝ /Internal examiner/፣ ለሊቀመንበር /Chairperson/ የሚከፈል ክፍያ በተመለከተ የዩኒቨርሲቲ የሴኔት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ /Sec/ በቁጥር Sec/2008 በቀን 18/12/2008 ዓ.ም በተላለፈ ውሳኔ መሰረት የሚከፈል መሆኑን፣
- በዩኒቨርሲቲው መምህራን ለሰሩበትና ክፍያ ለሚያስፈልጋቸው ሥራ ክፍያ የሚፈጽሙት በLEH (Lecture equivalent hour) በተላከ ስሌት ሲሆን፣ መምህራኑም በአላቸው የአካዳሚክ ማዕረግ መሠረት የሚከፈለው የገንዘብ መጠን እንደሚወሰን፣ በዚሁ መሠረት መምህራኑ ያስተማሩበትንና ያማከሩበትን እንደዚሁም የድህረ ምረቃ ተመራቂ ተማሪዎችን የፈተኑበትን የሥራ ጫና ወደ LEH በመቀየርና እንደየአካዳሚክ ማዕረጋቸው በተቀመጠው "Rate" በማብዛት ክፍያዎቹ የተፈጸሙ መሆናቸውን፣

  በምላሹ ገልጿል፡፡

3.1.2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ከመደበኛ በጀት የወጣው ሂሳብ በመንግሥት መመሪያ በወጣ ተመን መከፈል ነበረበት፡፡ ከውስጥ ገቢ የተከፈለውም በመመሪያው መሠረት በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ውሳኔ መፈጸም ነበረበት፡፡ በመሆኑም ክፍያዎቹ በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸመ በመሆኑና የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኖ ስላልተገኘ በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለት፡፡

3.1.3 <u>የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>
<u>የጤና ባለሙያዎች የተረኝነት አበል ክፍያ፣</u>

3.1.3.1 <u>ግኝት</u> ፣

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የጠቅላይ ሚኒስተር ጽ/ቤት ሰኔ 17 ቀን 2005 ዓ.ም ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በፃፈው የደብዳቤ ቁጥር መ200-813/6 ለጤና ባለሙያዎች በየተረኝነት አበል ክፍያ የተፈቀደ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ **በሪፈራል ሆስፒታል** በድምሩ **ብር 185,109.75** ክፍያ ሲከፈል ወሩን መሉ ቀንም ማታም የጤና ባለሙያዎቹ ስራ ገብተው ስለመስራታቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ሰነድ ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ (የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቁጥር 9 ቀርቧል፡፡)

3.1.3.2 ስጋት ፣

ለክፍያው በቂ ማስረጃ አለመቅረብ የሂሳቡን ትክክነኛነት ማረጋገጥ አያስችልም ፡፡

3.1.3. 3 **የማሻሻያ ሃሳብ** ፣

የጤና ባለሙያዎች የተረኝነት አበል ክፍያ ሲፈጸም ወሩን መሉ በቀን እና በማታ የስራ ፕሮግራም በስራ ገብታቸው ስለመስራታቸው የሚያመለክት የሰዓት መቆጣጠሪያ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ካልሆነም ሂሳቡ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.1.3. 4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

የሥራ አመራሩ፣ **የሪፈራል ሆስፒታል** የጤና ባለሙያዎች የተረኝነት አበል ክፍያ ሲከፈል የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም ለተባለው በሪፈራል ሆስፒታል **ለ** school medicine department of surgery, neuron surgery unit and orthopedics unit ባለሙያዎች ለሆስፒታል አገልግሎት በኮንትራት ቀጥረው ያሰሩት ከፍተኛ የታማሚ ቁጥር ስላለባቸው እና ምንም ቋሚ ሰራተኛ በዘርፉ የሌለ በመሆኑ ሲሆን ባለሙያዎቹ ስራ ገብተው ለመስራታቸው የሰአት መቆጣጠሪያ ሰነድ /ፎርም/ የ30 ቀን የ **JV 527101 እና የ JV 527102** ኮፒ አድርገው ያያዙ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.1.3.5 **የኦዲተሩ አስተያየት፣**

ከምላሹ ጋር ቀርቧል የተባለው የሰአት መቆጣጠሪያ ሰነድ /ፎርም/ ስላልቀረበ በማሻሽያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

## 3.1.4 ለትምህርት ወደ ውጪ ሃገር ለሄዱ መምህራን አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ እና ተያያዥ ክፍያዎች፣

3.1.4.1 ግኝት፣

ለትምህርት ወይም ሥልጠና በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር ተልከው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሠራተኞች ደመወዝ አከፋፈልን በተመለከተ፣ እስከ አንድ ወር ለሚቆይ ጊዜ ወደ ውጭ ሀገር ለሚሄዱ ሙሉ ደመወዛቸው እንዲከፈል ሆኖ ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ጊዜ የሚሄዱት ግን ከተፈላጊ መረጃዎች ጋር ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ሲፈቀድ በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው እንደሚከፈላቸው ሚያዝያ 20/1990 በቁጥር 80-አጠ52/01/09 ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት መመሪያ መተላለፉ ተገልጾ መስከረም 22/1993 በቁጥር መ19/ጠ49/2/56 ከቀድሞ የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን መመሪያው የተላለፈ ቢሆንም፣

- **በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ** ግማሽ ደመወዝ መከፈል ሲገባ ሙሉ ደመወዝ በመከፈሉ በድምሩ **ብር 91,385.00** አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ መኖሩ፣ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 10 ተመልክቷል፡፡)
- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** ግማሽ ደመወዝ መከፈል ሲገባ ሙሉ ደመወዝ በመከፈሉ ብር **281,127.00** ደመወዝ ያለአግባብ፣ ሰዎቹ ውጭ ሀገር ትምህርት ላይ እያሉ ብር 11,517.00 የአኑዋላይዜሽን፣ ብር 2,000.00 የትራንስፖርት አበል፣ ብር 32,000.00 የቤት አበል እና ብር 7,500.00 የሃላፊነት አበል፣ በድምሩ ብር **334,144.00** አለአግባብ የተከፈለ መሆኑ፣ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 11 ተመልክቷል፡፡)

በአጠቃላይ በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር የተላኩ መምህራን ሙሉ ደመወዝ፣ አኑዋላይዜሽን፣ የትራንስፖርት አበል፣ የቤት አበል እና የሃላፊነት አበል በመከፈሉ በድምሩ **ብር 425,529.00 (91,385.00 + 334,144.00)** ከመመሪያ ውጭ አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

3.1.4.2 <u>ስጋት</u>፣

የመንግሥት ገንዘብ ለግለሰብ ጥቅምና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.1.4.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ከመመሪያ ውጪ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም በደመወዝ ክፍያ ወቅት አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

3.1.4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

የሥራ አመራሩ፣

- **በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፡-** ለስልጠና የሄዱት ውጪ ሀገር ሳይሆን በሀገር ውስጥ ሆኖ ወደ ውጪ ሀገር ለ1 ወር ለሳንድዊች ኘሮግራም ብቻ ሄደው የሚመጡ በመሆኑ መመሪያ ከሚፈቅደው ወጪ የተከፈለ ገንዘብ አለመኖሩን፣
- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፡-**

1. አቶ ደሳለኝ ጀዊሶ፣ አቶ አንዳርጋቸው መኮንንና አቶ እሸትአየሁ ክንፉ በEthio-German Home Grown PhD program በተለያዩ የትምህርት መስክ ተመልምለው በሀገር ውስጥ ተባባሪ አማካሪዎች በሚገኙባቸው ዩኒቨርሲቲዎች ተመዝግበው እንደሚማሩና ዲግሪያቸውም ከሚመዘገቡበት የሀገር ውስጥ ዩኒቨርሲቲ የሚሰጥ መሆኑን የፌደራል ትምህርት ሚ/ር ሚያዝያ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር 7/2-4303/641 በተፃፈ ደብዳቤ መግለጹን እና ተጠቃሾቹ በጀርመን ሀገር የሚቆዩት ለጥቂት ወራት ብቻ በመሆኑ መምህራኖቹ እንደ ሀገር ውስጥ ተማሪ ተቆጥረው ጥቅማጥቅማቸው እንዲከበርላቸው ባቀረቡት መሰረት ሀገር ውስጥ ለሚማር በድህረ ምረቃ ተማሪ የሚከፈለው የትምህርት ጥቅማጥቅም እንዲከፈላቸው ከአካ/ጉ/ም/ኘ/ጽ/ቤት በተወሰነው መሰረት ክፍያው መፈጸሙን፣ ተጠቃሾቹ ወደ ውጭ ሀገር ሲሄዱ የሚቋረጥ እንደሆነ፣ በአሁኑ ወቅት ተጠቃሾቹ እንደ ሀገር ውስጥ ተማሪ ስለሚታሰቡ የትምህርት ውላቸው እንደ ሀገር ውስጥ ተማሪ እንደገና ተስተካክሎ መፈረሙን፣ ነገር ግን ወደ ጀርመን ሀገር ሲሄዱ ሙሉ ሲከፈላቸው የነበረው ደመወዝ ግማሽ ተደርጎ እየተከፈላቸው መሆኑን፣

   አቶ እስጢፋኖስ ዮሐንስ ለትምህርት ውጭ ሀገር ሲሄዱ ከመስከረም ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዛቸው ግማሽ ሆኖ ሊከፈላቸው ይገባ ስለነበር ከመስከረም እስከ ሕዳር ወር 2009 ዓ.ም ድረስ ያለአግባብ የተከፈላቸው ደመወዝና አንዋላይዜሽን ተሰልቶ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ የሚደረግ መሆኑን፣በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.1.4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

- ከህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለስልጠና የሄዱት ውጪ ሀገር ለ1 ወር ለሳንድዊች ኘሮግራም ብቻ ሄደው የሚመጡ ለመሆናቸው በምላሹ የተገለጸ ቢሆንም ውጭ ሀገር የቆዩበት እና ሀገር ውስጥ የቆዩበት ጊዜ ተለይቶ ማስረጃ ስላልቀረበለት ምላሹ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተለይቶ ሊጠራ የሚችል ከሆነ ተጣርቶ፣ ካልተቻለም እንዳለ፣ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡
- ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የአቶ ደሳለኝ ጀዊሶ፣ አቶ አንዳርጋቸው መኮንን እና አቶ እሸትአየሁ ክንፉን በተመለከተም በጀርመን ሀገር የሚቆዩት ለጥቂት ወራት ብቻ በመሆኑ

መምህራኖቹ እንደ ሀገር ውስጥ ተማሪ ተቆጥረው ጥቅማጥቅማቸው እንዲከበርላቸው ባቀረቡት መሰረት ሀገር ውስጥ ለሚማር በድህረ ምረቃ ተማሪ የሚከፈለው የትምህርት ጥቅማጥቅም እንዲከፈላቸው በተወሰነው መሰረት ክፍያው መፈጸሙ በምላሹ የተገለጸ ቢሆንም ጀርመን ሀገር የቆዩበት እና ሀገር ውስጥ የቆዩበት ጊዜ ተለይቶ ማስረጃ ስላልቀረበለት ምላሹ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ይህም ቢሆን ተለይቶ ሊጠራ የሚችል ከሆነ ተጣርቶ፣ ካልተቻለም እንዳለ፣ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

3.1.5 <u>ለቴክኒካል አሲስታንስ አለአግባብ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ የቤት አበል</u>፣

3.1.5.1 <u>ግኝት</u>፣

የአካዳሚክ ባለሙያዎች ጥቅማጥቅም ክፍያን አስመልክቶ በቀን 06/01/2006 ዓ.ም በቁጥር መ/90-1013/2 ከኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ የአመራር አካላትና የአካዳሚክ ባለሙያዎች የቤት አበል ለረዳት ፕሮፌሰር እና በላይ ብር 1,000.00፣ ለረዳት ሌክቸረርና ሌክቸረር ብር 800.00፣ ለረዳት ምሩቅ I እና II ብር 600.00 የተፈቀደ ቢሆንም፡

- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** ለቴክኒካል አሲስታንስ I፣ II እና III በመመሪያው ከተፈቀደው ውጭ ብር 250.00 እና 239.81 ተመን በመፍቀድ በድምሩ ብር 281,046.31 አለአግባብ የቤት አበል የተከፈላቸው መሆኑን፣
  (ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቁጥር 12 ቀርቧል)

3.1.5.2 <u>ስጋት</u> ፣

ክፍያው የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ከመዳረጉም ባሻገር የመንግስት መመሪያዎች እና ደንቦች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ በማድረግ ለሌሎች ብልሹ አሰራሮች በር ሊከፍት ይችላል፡፡

3.1.5.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

ክፍያው ከመመሪያ ውጭ በመሆኑ እንዲቆም ማድረግ እና በኦዲት ናሙና ከተገለጸው በተጨማሪ ሌላ አላግባብ የተከፈለ ተመሳሳይ ክፍያ በሙሉ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ማናቸውም ክፍያ ሲፈፀም በመንግስት የክፍያ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ሊፈፀም ይገባል፡፡

3.1.5.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

የሥራ አመራሩ፣

- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** የቴክኒካል አሲስታንቶች የቤት ኪራይ አበል ከዚህ ቀደም ሲከፈላቸው መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን በአሁን ወቅት ግን ክፍያው የተቋረጠ መሆኑን፣

3.1.5.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>፣

- በአሁን ወቅት ግን ክፍያው የተቋረጠ ለመሆኑ በምላሹ የተገለጸ ቢሆንም ቀደም ሲል የተከፈለው (በግኝቱ የተጠቀሰው) ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.1.6 <u>ዘላቂነት ባለው የስራ መደቦች ላይ በቀን ሰራተኝነት የተቀጠሩ ሰራተኞችን በተመለከተ</u>፣

3.1.6.1 <u>ግኝት</u> ፣

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ18/22/459 በቀን 16/04/2005 ዓ.ም በኮንትራት /በጊዜያዊ ተቀጥረው የሚገኙ ሰራተኞችን ቋሚ ለማድረግ በወጣው አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ እንዲሰናበቱና ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ቅጥር እንደማይፈፀም እንዲሁም ቅጥር ፈጽሞ የተገኘ የስራ ሃላፊ በህጉ መሰረት ተጠያቂ እንደሚደረግ ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ በፋሲሊቲ ዳይሬክቶሬት ሥራ ላሉ ለጽዳት እና አትክልተኛ፣ በጥገና ዳይሬክቶሬት ለሁለገብ ጉልበት ሰራተኞች እንዲሁም በተማሪዎች አገልግሎት ለጽዳት፣ ለግቢ ውበት፣ መስተንግዶ፣ ውሃ ኦፐሬተር፣ መኝታ ተቆጣጣሪ ሰራተኞች ቀጣይነት እና ዘላቂነት ባላቸው የስራ ዘርፎች ቋሚ የስራ መደብ እንዲሆኑ ጥናት በማድረግ መዋቅር በሚስቴሩ በማስፈቀድ ክፍያውን መፈጸም ሲገባ በቀን ሰራተኝነት የተለያየ የክፍያ ተመን በማድረግ **በዋናው ግቢ** በድምሩ ብር 2,998,053.14 (ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቁጥር 14 ቀርቧል) እና **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** በድምሩ ብር 397,158.50 (ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቁጥር 15 ቀርቧል)፣ በአጠቃላይ በድምሩ **ብር 3,395,211.64** የተከፈለ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በተጨማሪም ለቦታው የሚያስፈልገው የሰው ሃይል በጥናት ባልተደረሰበት ሁኔታ ከፍተኛ የሰው ሃይል በመጠቀም ክፍያው ወጪ ቆጣቢ አሰራርን እና መመሪያን ያልተከተለ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3.1.6.2 <u>ስጋት</u> ፣

- መመሪያን መጣስ ተጠያቂነትን ያመጣል፡፡
- ዘላቂነት ባላቸው የስራ መደቦች ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት የሰው ሃይል በእቅድ እንዳይመራና በዜጎችና በመንግስት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.1.6.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

- ማናቸውም ክፍያዎች የመንግስት ደንብና መመሪያ የተከተሉ መሆን አለባቸው፡፡ በመሆኑም ዘላቂነት ባለው የሥራ ዘርፍ  በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ ጊዜ ሳይሰጠው  በስራ ዘርፎቹ ላይ ጥናት በማድረግ ቋሚ የስራ መደብ እንዲያገኙ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴርን ጠይቆ በማስፈቀድ ሲፈቀድ ክፍያው ሊፈጸም ይገባል፡፡
- ለወደፊቱ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት /ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴርን በማሳወቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.1.6.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ፣

- **በዋና ግቢ** የቀን ሠራተኞች ቅጥር የተከናወነበት ምክንያቶች እንደሚከተለው፡-
  - ➢ በሥራ ክፍሎቹ ቋሚ ሠራተኛ ለመቅጠር የመዋቅር ጥበት በመኖሩ፣
  - ➢ በ2009 ዓ.ም ተጨማሪ/አዲስ የስራ መደቦችን ጥያቄ ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አቅርበው እንዳያስወስኑ አዲሱ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን (JEG) ሥርዓት ተግባራዊ እየተደረገ ስለሆነ ይህ ሥራ ከተጠናቀቀ በኃላ አዲስ (ተጨማሪ) የሥራ መደቦችን ማስፈቀድ እንደሚችሉ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተነገራቸው ስለሆነ፣
  - ➢ ባሉት ቋሚ ሠራተኞች ብቻ ሥራውን መሸፈንና የመማር ማስተማር ሂደትን፣ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሥራን፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራን እንዲሁም የአስተዳደር አገልግሎት ሥራዎችን ማሳለጥና ማሳካት አስቸጋሪ ሆኖ ስለተገኘ
- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፡-**

- በኢንሲትቲዩቱ ውስጥ በ2007 ዓ.ም መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በጥቃቅንና በአነስተኛ ማህበራት የተደራጁ ማህበር ቁጥራቸው በ7 ማህበራት የተደራጁ ቁጥራቸው 70 የሚሆኑ ሰራተኞች ተደራጅተው ከመንግስት አካል በተላከላቸው መሰረት በተማሪዎች ምግብ ቤት፣ ተማሪዎች መኝታ አገልግሎት፣ በተማሪዎች መማሪያና አከባቢ ፅዳት እንድሠሩ የተቀጠሩ መሆናቸውን፣
- የኢንስቲትዩቱ አስተዳደራዊ መዋቅር በ2007 ዓ.ም ሲፀድቅ አንደንድ ለተቋሙ ስራ በቀጥታ የሚያግዙ መደቦች ለምሳሌ እንጨት ፈላጭ፣ ሁለገብ የጉልበት ሠራተኞች መደብ ተጠይቀው በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በኩል ከስራው ስፋትና ጫና አንጻር በበቂ ቁጥር ባለመጽደቁና ባለመፈቀዱ ምክንያት የተቀጠሩ ሰራተኞች መሆናቸውን፣
- በተጨማሪም ዘላቂነት ባላቸው  መደቦች ላይ በተለይ በጥገና ክፍል በሚገኙ የስራ መደቦች በኤሌክትረሽያን፣ በውሃ ቧንቧ ሥራዎች እና በፍሳሽ መስመር እና በመሳሰሉት ሥራ መደቦች ቢኖሩም አብዛኞዎቹ የሙያ መስመሩን ከፍ አድርጎ የሚጠይቅና እንድሁም የCOC ውጤት በመጠየቃቸው ምክንያት ብዙ ጊዜ ባለሙያዎች በገበያ በማጣት ከሥራ አንገብጋቢነትና ጊዜ የማይሰጥ በመሆኑ በቀን ሥራ ሰራተኞችን ቀጥሮ በማሰራት ወቅታዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ማስቻሉን፣

ከላይ በተገለፁ አስገዳጅ ምክንያቶች በሥራ ክፍሎቹ የቀን ሠራተኞች ቅጥር በተፈላጊ ችሎታ መስፈርት እና በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የደመወዝ ስኬል መሠረት እየተፈፀመ ስራው እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰው የተጀመረው አዲሱ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን (JEG) ሥራ እንደተጠናቀቀ አዲስ (ተጨማሪ) የሥራ መደቦችን በማስፈቀድ የሥራ መደቦቹም በቋሚ ሠራተኞች የሚሞሉ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

### 3.1.7 <u>ከውጭ ሀገር መምህራን ደመወዝ ላይ ያልተቀነሰ የስራ ግብር፣</u>

#### 3.1.7.1 <u>ግኝት</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በቀን 01/10/09 ቁጥር ተ/ዲ/ቀ/1/277 በሠጠው ማብራሪያ በተቀጣሪ መምህራን አገርና በኢትዮጵያ መካከል በተፈረሙ ስምምነቶች መሠረት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት ከፈረንሳይና ከህንድ ጋር የተደራራቢ ግብር ማስወገድ ስምምነት ተፈፅሞና ፀድቆ ተፈፃሚ እየተደረገ ሲሆን በዚህ ስምምነት ውስጥ በሙያው አገልግሎት እየሠጠ ያለ ተመራማሪ/አስተማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት ለመስጠት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ቀን አንስቶ ከሁለት አመታት ላልበለጠ ጊዜ ከግብር ነፃ መሆኑ የተገለፀ

በመሆኑ ከሁለት ዓመት በላይ ከሆናቸው በመመሪያው መሰረት የስራ ግብር የተቀነሰ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከዩኒቨርሲቲው ለኦዲት ተጠይቆ በቀረበው የህንድ መምህራን መረጃ መሰረት ከሁለት ዓመት በላይ ለሆናቸው የወር ደመወዝ ሲከፈል የስራ ግብር መቀነስ ሲገባው በበጀት ዓመቱ ብር 5,193,350.12 መቀነስ እና ለሚመለከተው መ/ቤት ገቢ መሆን የነበረበት የስራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

(ዝርዝር ሁኔታው ከታች በአባሪ 16)

### 3.1.7.2 ስጋት

ዩኒቨርሲቲው ከመንግስት ህግና ደንብ ውጭ ለውጭ መምህራን ክፍያ መፈፀሙ ውስን የሆነው የመንግስትና የህዝብ ሀብት ለህንድ ሀገር መምህራን እንዲዉል ሆኗል፡፡

### 3.1.7.3 የማሻሻያ ሃሳብ

- ዩኒቨርሲቲው አላግባብ የከፈለው ክፍያ ተገቢ ባለመሆኑ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ እና ተመላሽ የተደረገውም ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡
- ለወደፊቱም ተመሳሳይ ዓይነት ክፍያ እንዳይፈፀም ተገቢ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

### 3.1.7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ፣

አንድ የህንድ መምህር ውል ሲገባ ለመጀመሪያ ዓመት እስከ ነሐሴ ለሁለተኛ ዓመት እስከ ሐምሌ ወር እ.ኤ.አ. በመሆኑ በሁለት የሥራ ስምምነት ውል መካከል ውሉና ክፍያው ለሁለት ወራት ስለሚቋረጥ ውሉ ተከታታይነት የለውም የሚለውን ዕሳቤ በመያዝ ክፍያው ሲፈፀም የቆየ ቢሆንም ከዩኒቨርሲቲው በቀን 16/05/10 ዓ.ም በቁጥር ሀዩ/02/9044/10 በተፃፈ ደብዳቤ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መ/ቤትን ስለ ውጭ መምህራን የሥራ ግብር በተመለከተ ማብራሪያ በመጠየቅ እንዲሁም ማብራሪያው እስኪመጣ ድረስ ከአዲስ የውጭ መምህራን ተቀጣሪዎች በስተቀር ከሌሎች የውጭ መምህራን የሥራ ግብር ከታህሳስ ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ በህጉ ማብራሪያው እስኪመጣ ድረስ የተጠበቀ ሲሆን በቁጥር ገ/ኢ/ቀ/5/219 በቀን 30/05/10 ዓ.ም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በተላከው ማብራሪያ መሠረት የሥራ ግብር ሥርዓት በአግባቡ እየተፈፀመ መሆኑን እና ለወደፊቱም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል፣

በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.1.7.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

- የሥራ ግብሩን አቀናነስ በተመለከተ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተጠይቆ የመጣው በጥር ወር 2010 መሆኑ በምላሹ የተጠቀሰ ቢሆንም ከሀምሌ 1/2008 ጀምሮ በተገኘ ገቢ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተጠቅሶ በወጣው የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) መሠረት ከገቢ ግብር ነጻ ከሆኑ ገቢዎች አንዱ በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ከግብር ነጻ የሆነ ገቢ በመሆኑ እና ይህ በሌለበት የገቢ ግብሩ አለመቀነሱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በተላከው ማብራሪያ መሠረት የሥራ ግብር ሥርዓት በአግባቡ እየተፈፀመ መሆኑን እና ለወደፊቱም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የተጠቀሰ ቢሆንም በግኝቱ የተጠቀሰው ከገቢ ግብር ነጻ ለመሆኑ የተፈቀደበት ማስረጃ ስለሌለ በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

3.2 <u>የእቃና አገልግሎት ግዥ</u>፣

3.2.1 <u>አቅራቢዎች ሳይወዳደሩ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ፣</u>

3.2.1.1 <u>ግኝት</u>፣

ሰኔ/2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ግዢዎች በመመሪያው መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- **በዋናው ግቢ** በድምሩ የብር 16,954,994.98 የተለያዩ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ጥንድ አልጋ፣ ሎከር፣ ቴብል ቼር፣ ጠረጴዛ እና የብር 4,565,958.00 ስጋ፣ በድምሩ የብር 21,520,952.98 ግዥ፣
- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** በድምሩ የብር 1,495,920.00 የስጋ ግዥ፣
- **ግብርና ኮሌጅ** ብር 727,280.00 የስጋ ግዥ፣

በአጠቃላይ ድምር የብር 23,744,152.98 የስጋ እንዲሁም የተለያዩ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ጥንድ አልጋ፣ ሎከር፣ ቴብል ቼር፣ ጠረጴዛ ከዩኒቨርሲቲው ኢንተርፕራይዝ ያለውድድር ግዥው በቀጥታ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ (የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ 18 ቀርቧል፡፡)

3.2.1.2 ስጋት፣

ግዥ በመመሪውያ መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም:: የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥም ይችላል፡፡

3.2.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

- ዩኒቨርሲቲው ማናቸውንም የእቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጽም በመንግስት የግዥ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሊፈጽም ይገባል፡፡
- የዚህ አይነት አሰራር የመንግስትን ጥቅም የሚያሳጣ አሰራር ስለሆነ ዩኒቨርሲቲው በቀጥታ ግዥ ሲፈጽም በልዩ ሁኔታ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ ሲፈቀድለት ግዥውን ሊፈጽም ይገባል፡፡

3.2.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ፣

- **ዋና ግቢ፡-** በ2009 በጀት ዓመት ለዋናው ግቢ እና ለወንዶገነት ካምፓሶች የአዲስ ተማሪ ቁጥር በመጨመሩ ምክንያት ለተማሪዎች ፋሲሊቲ ለማሟላት ቁሳቁሱን ለማቅረብ ጨረታ ይውጣ ሲባል ቢያንስ ሁለት ወር የሚወስድ በመሆኑ ይህን ያህል ጊዜ ይጠበቅ ሲባል በመማር ማስተማሩ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር ስለሆነ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ የመንግስት ስለሆነ በአስቸኳይ እንዲቀርብም ተፅዕኖ ማሳደር ስለሚቻል ለመቆጣጠር አመቺ ስለነበር በግ/አዋጅ አንቀፅ 51 (1) (ሸ) መሰረት ግዥውን ለመፈጸም መገደዳቸውን፣ ይሁን እንጂ ይህን ዓይነት ግዥ በ2010 በጀት ዓመት ግልጽ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ በውድድር እንዲፈጸም ከወዲሁ መደረጉን፣
- **ዋና ግቢ፡-** ከተማሪዎች ቀለብ ግብዓት አቅርቦት መካከል ስጋ ከፍተኛ የተማሪ ጩኸት የሚያስነሳ የምግብ ግብዓት በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ዘመናዊ ቄራ በማደራጀት የእርድ ከብት በዚሁ ቄራ እንዲፈጸም ሲያደርግ መቆየቱን እና ይህንንም አሰራር የተማሪዎች ተወካዮች በየጊዜው እንዲቆጣጠሩ በማድረግ እየተሰራበት መሆኑን፣ በ2009

በጀት ዓመትም ግልጽ ጨረታ አውጥተው የራሱ የሆነ ቁራ ያለው ድርጅት ማግኘት አለመቻሉን፣ የተማሪውን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የኢንተርፕራይዙን አቅርቦት ዋጋ ከግልጽ ጨረታ ከተገኘው ዋጋ ጋር በማነጻጸር አማካኝ ዋጋ በመተመን ኢንተርፕራይዙ በቅርበት የራሱ ቁራ ስላለው እንዲያቀርብ መደረጉን፣ በ2010 በጀት ዓመት ግልፅ ጨረታ እንዲወጣ ተርጎ በዚህም መሰረት እየተሰራበት እንደሚገኝ፣

- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት**

ኢንስቲትዩቱ በተዘጋጀው የተማሪዎች የምግብ ሜኑ መሰረት በሳምንት ሶስት ጊዜ የስጋ አቅርቦት ከዩኒቨርሲቲው ገቢ ማመንጫ ኢንተርኘራይዝ ኃላ/የተ/የግል ማህበር እየወሰዱ ግዥ እንደሚፈጸም፣ ከኢንተርኘራይዙ በቀጥታ ግዥ የሚፈፅሙበት ምክንያት ለተማሪዎች አገልግሎት የሚሆን ስጋ አቅርቦት በግልፅ ጨረታ አቅራቢዎች እንዲወዳደሩ የተጋበዙ ቢሆንም የተማሪዎችን ጤናና ደህንነት ሊጠብቅ የሚችል ዘመናዊ ቁራ ያላቸው ድርጅቶች ባለመገኘታቸውና በተጨማሪም ከተማሪዎች ወርሃዊ የምግብ በጀት አንፃር የስጋ ዋጋው የሚገር መሆኑ ከግንዛቤ በማስገባት መሆኑን፣ በዚሁ መሰረት ኢንተርኘራይዙ የራሱ ዘመናዊ ቁራ ያለው በመሆኑና የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ካውንስልም በተመነው ዋጋ ሊያቀርብ የሚችል በመሆኑ ከተማሪዎቹ የጤናና ደህንነት እንዲሁም የተሻለ ዋጋ ከመሆኑ አኳያ የተሻለ አማራጭ ባለመኖሩ ምክንያት ዩኒቨርሲቲው ባስቀመጠው አቅጣጫ ከኢንተርኘራይዙ የስጋ አቅርቦት እየወሰዱ በተወሰነው የአንድ ኪሎ ግራም ስጋ ዋጋ መሰረት እየተሰላ ከድርጅቱ የስጋ ግዥ እየፈፀሙ እንደሚገኙ፣

### 3.2.2 <u>አንድ ላይ በጨረታ መገዛት ሲገባ ተከፋፍሎ በዋጋ ማቅረቢያ የፈጸመ ግዥ፣</u>

#### 3.2.2.1 <u>ግኝት</u>፣

ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 24/1፣ እና አንቀጽ 24.3 ፊደል ሀ እና ለ፣ አንቀጽ 24.12 እንደ ቅደም ተከተላቸው፡ የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ ከታህሳስ 12/2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ በተሻሻለው የግዥ መመሪያ ለእቃ እስከ ብር 200,000.00፣ ለአገልግሎት ግዥ እስከ ብር 150,000.00 የሚገመቱ ግዢዎች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ መፈጸም እንደሚቻል፣ የመንግስት መ/ቤቱ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡት ሁሉም ተሳታፊዎች በዙር የመወዳደር እድል ማግኘታቸውን እና ለመ/ቤቱ ጠቃሚ የሆነ የተለየ ሁኔታ መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር አንድ

ወይም የተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ በተደጋጋሚ መጋበዝ እንደሌለባቸው፣ እንዲሁም የመንግስት መ/ቤቱ የዋጋ ማቅረቢያ በመስጠት እና ዋጋ በመወሰን ሂደት ሊፈጠር የሚችል መመሳጠርን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር በመከተል እና መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር፣ በግዥ ስራ ክፍሉ የሚካሄድ የገበያ ጥናትን በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማመን እና በየጊዜው ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ፣ የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት እንደሌለባቸው ይገልጻል፡፡

በዚሁ መሰረት በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተገዙት እቃዎችና አገልግሎቶች ኦዲት ሲደረግ፣

**በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣**

- ለኬሚካል፣ ለሲቪል ኢንጅነሪንግ፣ ለኤሌክትሪካል እና ለሜካኒካል ት/ክፍሎች የሚያገለግሉ በአንድነት በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም የሚገባቸው በድምሩ **የብር 5,314,995.80** የላቦራቶሪ ዕቃዎች ተከፋፍለው በዋጋ ማቅረቢያ የተገዙ መሆኑ፣ በተጨማሪም፣

➢ ተቋሙ በተደጋጋሚ በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በግዥ ሥራ ክፍሉ የገበያ ጥናት የማይደረግ እና በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ከሚወጣው ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኋላ ግዥው እየተፈጸመ አለመሆኑ፣

➢ እቃዎች በተፈላጊ ባህርያት ዝርዝር /Specification/ ለመቅረባቸው ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ወይም የጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ የጹሑፍ ማረጋገጫ ሳይቀርብ እቃዎቹ ገቢ የሆኑ እና ክፍያው የተፈጸመ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ (ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 19 ቀርቧል፡፡)

3.2.2.2 <u>ስጋት</u>፣

- ግዥ በመመሪውያ መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም:: የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥም ይችላል፡፡

- የገበያ ዋጋ ጥናት ተደርጎ በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ከሚወጣው ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ትክክለኛው የገበያ ዋጋ ሳይታወቅ የሚፈጸም ግዥ ዋጋው የተጋነነ እና መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርገው ይችላል፡፡

3.2.2.3 የ<u>ማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

- ዩኒቨርሲቲው ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በጥቅል ወይም በጅምላ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም  አለበት፡፡
- ዩኒቨርሲቲው በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች  በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት በማድረግ እንዲሁም በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገቢያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኃላ ከተሳተፉት አቅራቢዎች ውስጥ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ያቀረበው ዋጋ ጋር ተመሳክሮ ዋጋው የተጋነነ መሆኑን እና አለመሆኑን በማረጋገጥ ግዥውን መፈጸም አለበት፡፡

3.2.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ፣

**የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፡-**

- የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በአምስት ፋካልቲና በ19 ትምህርት ክፍሎች ተዋቅሮ ወደ 12 ሺህ የሚጠጉ ተማሪዎችን በቀን፣ በማታ፣ በእረፍት ቀናት እና በክረምት መርሃ ግብር በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ኘሮግራም ተቀብሎ እያስተማረ የሚገኝ ሲሆን በተጨማሪም ለአካባቢ ቢሮዎችና ትምህርት ተቋማት የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችንም እንደሚያከናውን እና በኢንትቲትዩቱ ስር የሚገኙ ትምህርት ክፍሎች ሥርዓተ-ትምህርት /ካሪኩለም/ መሰረት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ተግባር ተኮር መሆኑን፣
- ስለሆነም ለዚሁ ተግባር የሚያገለግሉ የተለያዩ ቤተ ሙከራዎች /ላብራቶሪዎች/ እና ወርክሾፖች እንደሚገኙ እና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አዲስ ላብራቶሪዎችም ተገንብተው በመጠናቀቅ ላይ እንደሚገኙ፣ በዚሁ መሰረት በየትምህርት ክፍሉ ለሚገኙ ላብራቶሪዎችና ወርክሾፖችን አስፈላጊ በሆኑ ቋሚና አላቂ የላብራቶሪ ቁሳቁሶች

የማሟላት ስራዎች በግልጽ ጨረታና በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴዎች ሲከናወኑ መቆየታቸውን፣

- በኦዲት ግኝቱ ላይ እንደተገለፀው በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸው ግዥዎች በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ተከፋፍለው መገዛት የሌለባቸው ቢሆንም ትምህርት ክፍሎች ለቤተ ሙከራዎችና ወርክሾፖች የሚያስፈልጋቸውን እቃዎች **አቅደው በወቅቱ ባለማምጣታቸው** የተፈጠረ ችግር ሲሆን ተማሪዎቹ የተግባር ትምህርቱን በካሪኩለሙ መሰረት ከሚያጡ ተገደው የፈፀሙ ግዥ መሆኑን፣
- ሆኖም ኢንስቲትዩቱ ከላይ የተገለፀውን ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ እንዲያስችል በተቋሙ ያሉትንና አዲስ የተገነቡትን ላብራቶሪዎችንና ወርክሾፖችን የሚያስተዳድርና የሚመራ ኃላፊ የሚያስፈልግ መሆኑን በመገንዘብ ኢንስቲትዩቱ በአካዳሚክ ገቨርናስ ስትራክቸር ውስጥ አካቶ መዋቅሩን በማፀደቁ አንድ የላብራቶሪ ኃላፊ በ2010 በጀት ዓመት መመደቡን እና ኃላፊውም የቤተ ሙከራና ወርክሾፖ የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች አሰባስቦና አደራጅቶ ከነስፔስፊኬሽናቸው አቅርቦ ግዥው በግልጽ ጨረታ እንዲገዛ የግዥ ሂደቱ እየተከናወነ እንደሚገኝ፣
- የገበያ ጥናትን በተመለከተ አስፈላጊ በሆነባቸው በማንኛውም ሁኔታ ጥናቱ የሚደረግ ቢሆንም አሁን እየተከናወነ ካለው በተሻለ ሁኔታ የገበያ ጥናት ሥራ መሰራት እንዳለበት፣
- በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ሳይረጋገጡ ገቢ የሆኑ እቃዎችን በተመለከተ፤ በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9 በተራ ቁጥር 2 እና 4 እቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህርያት ዝርዝር /specification/ መቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የጽሁፍ ማረጋገጫ መቅረቡን ክፍያው ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄ መሆኑን እንደሚገልጽ በተገለፀላቸው መሠረት፤
- የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ግዥና ንብረት አስተዳዳር ቡድን በሥራ ክፍሉ የግዥ ጥያቄዎች በሚቀርቡበት ጊዜ ግዥዎችን በማሰባሰብ በእቅድ ለመግዛት በየበጀት ዓመቱ እቅድ በማቅረብ ለማኔጂመነቱ አፀድቆ የሚንቀሳቀስ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም እነዚህን ግዥዎች ከማዕቀፍ ግዥ በሚፈፀምበት ወቅት የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች በሚሆኑበት ወቅት የICT ባለሙያ በመያዝ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ የተላከው ባለሙያ

የቀረቡትን እቃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በተዘጋጀው ፎርማት መሠረት ሲያረጋግጥ እቃዎች ወደ ኢንስቲትዩቱ ተንገዝው እንዲመጡ እንደሚደረግ፣

- ሆኖም አሁን የግዥ ክፍል እንደ ሥራ ክፍተት ያየው የማእቀፍ ግዥ የገንዘብ ክፍያ የሚፈፀመው እቃው ወደ እቃ ግምጃ ቤት ከገባ ከአምስት ቀናት በኂላ በመሆኑ የጥራት ኮሚቴ ያየባቸውን የቴክኒክ ማረጋገጫ ሰነዶችን የገንዘብ ወጪ ክፍያ ደብዳቤ በሚጻፍበት ወቅት አብሮ አያይዞ መላክ ሲገባው በክፍሉ ፋይል በማድረግ ከእቃ ግምጃ ቤት ወጪ በሚጠየቅበት ጊዜ የቴክኒክ ግምገማውን በማየት ወጪ የሚፈቀድ ሲሆን ከአሁን በኂላ ላለው አሰራር ይህንን በማስተካከል ክፍሉ የቴክኒክ ማረጋገጫዎችን ለሂሳብና በጀት ክፍል መላክ እንዳለበት መረዳታቸውን፣ በመሆኑም ያለውን የአሰራር ክፍተት ምንም እንኳን ጥራት ለሌላቸው እቃዎች ክፍያ እንዲፈፀም ያደረጉ ባይሆንም ለመጪው ለማረም እንደክፍተት መውሰዳቸውን፣

  በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.2.3 <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብ</u>፣

3.2.3.1 <u>ግኝት</u>፣

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስከጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪዉ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪዉን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪዉ በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ ይገልፃል፡፡

በዚህም መሠረት በዩኒቨርሲቲው የሚፈፀሙ ክፍያዎች መመሪያውን የተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 02/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 68321 በሂሳብ መደብ 6215 በ2008 በጀት አመት ለኮሌጁ አገልግሎት የሚዉሉ **የላብራቶሪ ዕቃዎችና ሪኤጀንቶች ግዥ ከጄኔቲክ ፋርማ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 129,600.00** ግዥ ለተካሄደበት ክፍያ ሲፈፀም እቃዉ ገቢ የሆነዉ በቀን ከሰኔ 28-30/2008 ሲሆን ነገር ግን ክፍያ የተፈፀመዉ በጀት አመቱን ሳይጠብቅ መሆኑ፣

- በቀን 02/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 68320 በሂሳብ መደብ 6215 በ2008 በጀት ዓመት **ለኮሌጁ አገልግሎት የሚሆኑ የላብራቶሪ ዕቃዎችና ሪኤጀንቶች ግዢ ከ መልቲላስ ሳይንቲፊክ ሆም ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 339,168.86** ግዢ ለተካሄደበት ክፍያ ሲፈፀም እቃዉ ገቢ የሆነዉ በቀን 29/10/2008 ሲሆን ነገር ግን ክፍያ የተፈፀመዉ በጀት አመቱን ሳይጠብቅ መሆኑ፣
- በቀን 27/11/08 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 68316 በሂሳብ መደብ 6211 **ዩኒቨርሲቲዉ የደንብ ልብስ ሸሚዝ ከ አየለች ዱሬሳ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት መደብር ብር 158,010.00 ግዢ ለተካሄደበት** ክፍያ ሲፈፀም አቃዉ ገቢ የሆነዉ በቀን 27/10/08 ሲሆን ነገር ግን ክፍያ የተፈፀመዉ በ2009 በጀት አመት መሆኑ፣

**ባጠቃላይ በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለ2008** በጀት ዓመት ለተፈጸመ ግዥ የሰራተኞች ደንብ ልብስ እና የላብራቶሪ እቃዎች ግዥ በበጀት እጥረት ምክንያት ሳይከፈል የቀረ በማለት በ2009 በጀት ዓመት በድምሩ **ብር 626,778.86** ተከፍሎ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

3.2.3.2 <u>ስጋት</u>፣

ዩኒቨርሲቲው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ በፈፀመበት እና አቅርቦቱን ባገኘበት በጀት ዓመት ሂሳቡ በወጪ አለመመዝገቡ የበጀት አጠቃቀሙን የተዛባ ያደርገዋል፡፡

<u>3.2.3.4 የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

- በ2009 በጀት ዓመት በዕቅድ ለተያዙ ስራዎች ማከናወኛ ከተፈቀደለት በጀት የቀድሞውን በጀት ዓመት ክፍያ መፈጸሙ ተቋሙ የበጀት ህጉን ተከትሎ አለማከናወኑን ያመለክታል፡፡
- በመሆኑም ክፍያዎች በወቅቱ እንዲከፈሉ እና ተገቢው የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል ፡፡

<u>3.3.3.4</u> <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>፣

ኮሌጁ በ2009 በጀት አመት ባጋጠመዉ የበጀት እጥረት ምክንያት በ2008 በጀት አመት መከፈል የሚገባቸዉ ክፍያዎች የግዥ ክፍያዎች በ2009 በጀት አመት በማኔጅመንት ዉሳኔ መሰረት ክፍያዎቹ መፈጸማቸውን ገልጿል፡፡

<u>3.2.3.5 .የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ለወደፊቱ በተቻለ መጠን ግዥዎችን በደንቡ መሠረት በጊዜ በመፈጸም ሂሳቡ በወቅቱ ተከፍሎ እንዲወራረድ፣ እንዲመዘገብና ሪፖርት እንዲደረግ መከታተል ያስፈልጋል።

4. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>፣

4.1 <u>በደንቡ መሠረት በወቅቱ ያልተወራረደ የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

4.1.1 <u>ግኝት</u>፣

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/4 ፊደል (መ) የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል። በዚህ መሰረት ኦዲት ሲደረግ ፡

<u>የመደበኛ በጀት ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- በልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያዎች ቅድመ ክፍያ ሂሳብ አርዕስት 4201 ብር 1,771,539.55 ከተለያዩ ግለሰቦች በወቅቱ መወራረድ ሲኖርበት ሳይወራርድ ወይም በጥሬ ገንዘብ ተመላሽ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፤
- ለግዥ ሠራተኛ የሚሰጥ ቅድመ ክፍያ ሂሳብ አርዕስት 4211 ብር **1,510,637.78** የሚታይ ሲሆን በዓመቱ መጨረሻ በግዥ ሠራተኞች ላይ የሚገኝ ሂሳብ መወራረድ ወይም ተመላሽ መሆን የነበረበት የመንግሥት ገንዘብ ተመላሽ ሳይደረግ በግዥ ሠራተኞች ስም የሚገኝ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 3,282,177.33 የመደበኛ በጀት ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ መወራረድ ሲኖርበት ያልተወራረደ መሆኑ፣

<u>የውስጥ ገቢ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- በልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያዎች ቅድመ ክፍያ ሂሳብ አርዕስት 4201 ብር 1,427,172.02 ከተለያዩ ግለሰቦች በወቅቱ መወራረድ ሲኖርበት ሳይወራርድ ወይም በጥሬ ገንዘብ ተመላሽ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፤
- በጥሬ ገንዘብ ጉድለት 4202 ብር 823,006.26 የሚገኝ መሆኑ፤
- ለግለሰቦች እና የግል ድርጅቶች ቅድመ ክፍያ በሂሳብ አርዕስት 4273 ብር 595,979.73 የተያዘ መሆኑ፣

በድምሩ 2,846,158.01 የውስጥ ገቢ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ ሲሆን በወቅቱ መወራረድ ሲኖርበት ያልተወራረደ ሂሳብ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ድምሩ **ብር 6,128,335.34 (ብር 3,282,177.33 የመደበኛ በጀት እና ብር 2,846,158.01 የውስጥ ገቢ)** በወቅቱ መወራረድ ሲኖርበት ያልተወራረደ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

4.1.2 <u>ስጋት</u>፣

ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ካልተወራረዱ ከቆይታ ብዛት ወደ ማይሰበሰቡበት ደረጃ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

4.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

በውዝፍ የሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ እንዲወራረድ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

4.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

የሥራ አመራሩ፣

- **በዋናው ግቢ 4201፡-**
  - **በዋናው ግቢ** በሰኔ 2009 የታየው ላይ ያልተወራረደው ብር 553,794.50 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 123,325.28 በፍርድ ቤት ዕልባት ያገኘ እና የሚወራረድ ቀሪው ብር 193,609.83 በየወሩ ከደመወዝ እየተቆረጠ ለሚመለከተው አካል ትራንስፈር እየተደረገ ያለ መሆኑን፣
  - **በቴክኖጂ ኢንስቲትዩት** ሰኔ 2009 የታየው ቀሪው ብር 159,184.00 ከደመወዝ እየተቀነሰ ተመላሽ እየተደረገ ያለ ሂሳብ ሲሆን ቀሪው ብር 418,465.68 እየተጣራ ያለ ሂሳብ መሆኑን፣
  - **በግብርና ኮሌጅ** ሰኔ 2009 የታየው ቀሪው ብር 190,246.37 እየተጣራ በ2010 በጀት ዓመት የሚወራረድ መሆኑን፣
  - **በጤና ሳይንስ ኮሌጅ** ሰኔ 2009 የታየው ቀሪው 335,062.00 በ2010 በጀት ዓመት እየተጣራ የሚወራረድ መሆኑን፣
  - **በወንዶ ገነት ኮሌጅ** ሰኔ 2009 የታየው ብር 114,787.00 ውስጥ 77,215.00 የኖክ ኢትዮጵያ ሊወራረድ ያልቻለ ስለሆነ ለማናጅመንት ለውሳኔ መቅረቡን እና ቀሪው እየተጣራ እንደሆነ፣

- **4211፡-** ሰኔ 2009 በ4211 በጀት ኮድ ላይ የታየው ብር 1,745,306.91 በፍርድ ቤት የተያዘ 1ኛ የአቶ ገዛኸኝ ያዳ ዕዳ ብር 1,118,447.06 2ኛ በአቶ ባቴኖ ባላ ስም ብር 198,859.69 መሆኑን፣

<u>**የውስጥ ገቢ ተሰብሳቢ ሂሳብ**</u>

- **4201**

➢ **በዋናዉ ግቢ** በሰኔ 2009 ብር 12,499.67 በየወሩ ከደመወዝ እየተቆረጠ ገቢ እየተደረገ ያለ እና ቀሪዉ ብር 93,673.67 ያልተወራረደ ሲሆን በማስታወቂያና በደብዳቤ በመግለጽ እንዲወራረድ ክትትል እየተደረገ እንደሚገኝ፣

➢ **በቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩት** ኮሌጅ በሰኔ 2009 የሚታየው ብር 184,202.32 በ2010 በጀት ዓመት የሚወራረድ መሆኑን፣

➢ **በጤና ሳይንስ ኮሌጅ** በሰኔ 2009 የሚታይ ብር 142,812.26 ሂሳብ እየተጣራ በ2010 በጀት ዓመት የሚወራረድ መሆኑን፣

➢ **በሪፈራል ሆስፒታል** በሰኔ ወር 2009 ብር 473,494.76 የሚታይ ሲሆን ብር 278,087.87 በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶ ውሳኔ ተሰጥቶ አፈጻጸም ላይ ያለ ሲሆን ቀሪው ብር 195,406.89 በ2010 በጀት ዓመት እየተጣራ የሚወራረድ መሆኑን፣

➢ **በወንዶ ገነት ኮሌጅ** በሰኔ ወር 2009 ብር 520,489.34 የሚታይ ሲሆን ሂሳቡ እየተጣራ በ2010 በጀት ዓመት እልባት የሚያገኝ መሆኑን፣

- **4202**

➢ **በዋናው ግቢ** በሰኔ 2009 የሚታይ ብር 823,006.26 የገንዘብ ጉድለት ሲሆን በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶ በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን፣

- **4273**

➢ **በሪፈራል ሆስፒታል** በሰኔ 2009 የሚታይ ብር 595,979.73 የዱቤ ህክምና የተሰጠበት ሲሆን ሃዋሳ ጨርቃጨርቅና ሃዋሳ ዙሪያ ዶሬ ባፋና ወረዳ ሊከፍሉ ባለመቻሉ በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶ በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን፣

4.1.5 <u>**የኦዲተሩ አስተያየት፣**</u>

- ያልተወራረዱ ሂሳቦች በማሻሻያ ሃሳቡ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ጉዳያቸው በህግ የተያዘውም ቢሆን የመጨረሻ እልባት እስኪያገኙ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

5. <u>**ተከፋይ ሂሳብ ፣**</u>

## 5.1 በወቅቱ ለባለመብቱ ያልተከፈለ ሂሳብ፣

### 5.1.1 ግኝት ፣

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8/5 ፊደል ሀ መሠረት ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸው የሚያረጋግጥ በቂ መረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡-

መደበኛ በጀት ተከፋይ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ ከሚታይ ብር 100,445,280.59 የመደበኛ በጀት ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ፣

- በልዩ ልዩ ደመወዝ ተቀናሽ በሂሳብ አርዕስት 5002 ብር 1,824,879.03፣
- በ5004 ብር 676,636.03፣
- በ5028 ብር 59,462.75፣
- በ5035 ብር 94,186.38፣

በድምሩ ብር **2,655,164.19** በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ሲሳብ መሆኑ፣

የውስጥ ገቢ ተከፋይ ሂሳብ ብር የሚታይ ሲሆን ከዚህ ውስጥ

በበጀት ዓመቱ ከሚታይ ብር 6,968,383.23 የውስጥ ገቢ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ፣

- በልዩ ልዩ ደመወዝ ተቀናሽ በሂሳብ አርዕስት 5002 ብር 6,716,124.98፣
- በ5005 የተያዘ ብር 16,541.64፣
- በሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች በሂሳብ አርዕስት 5054 ብር **87,000.00**፣

በድምሩ ብር **6,819,666.62** በውዝፍ የሚታይ ሲሆን በተጨማሪም በሂሳብ አርዕስት 5054 ለተያዘ ብር **87,000.00** በተከፋይ ሂሳብ ለመያዝ የሚያስችል ማስረጃ የሌለው መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

### 5.1.2 ስጋት፣

ተከፋይ ዕዳዎች በወቅቱ ካልተከፈሉ በቆይታ ብዛት ከፍተኛ የዕዳ ክምችት ሊኖር ስለሚችል ተቋሙን ለጉዳት ሊዳርግ ይችላል፡፡

### 5.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

የዕዳ ክምችት እንዳይኖር ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲከፈሉ የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

### 5.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣፣

የሥራ አመራሩ፣

- 5002
  - **በዋናው ግቢ** ሰኔ 2009 በ5002 በጀት ኮድ ላይ የሚታየው ብር 636,017.97 ላይ ብር 435,144.91 የተወራረደ እና ብር 133,023.89 በየወሩ ከደመወዝ ተቀንሶ ለባንክ የሚተላለፍ ሲሆን ቀሪው ብር 67,849.17 እየተጣራ ያለ ሂሳብ መሆኑን፣
  - **በጤና ሳይንስ ኮሌጅ** ሰኔ 2009 የታየው ብር 907,904.43 ላይ በ2010 በጀት ዓመት ብር 803,244.00 የተከፈለ ሲሆን ቀሪው ብር 104,657.49 በ2008 በጀት ዓመት አስተያየት የተሰጠበት ብር 92,653.86 እና እየተጣራ ያለ ሂሳብ መሆኑን፣
  - **በአዋዳ ካምፓስ** ሰኔ 2009 የታየው ብር 5,066.44 ላይ ብር 1,189.86 የተከፈለ ሲሆን ቀሪው ብር 3,877.04 እየተጣራ ያለ ሂሳብ መሆኑን፣
  - **በወንዶ ገነት ኮሌጅ** ሰኔ 2009 የታየው ብር 59,957.99 ሁሉም መከፈሉን፣
  - **በሪፈራል ሆስፒታል** ሰኔ 2009 የታየው ብር 23,509.84 ለውስጥ ገቢ ተከፋይ ስለነበረ ሁሉም ትራንስፈር መደረጉን፣
  - **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** ሰኔ 2009 የታየው ብር 192,422.36 ላይ ብር 145,127.36 ተከፍሎ ቀሪው ብር 47,295.00 እየተጣራ ያለ መሆኑን፣

  በአጠቃላይ በዩኒቨርሲቲው ሰኔ 2009 በ5002 በጀት ኮድ ከታየው ብር ላይ 1,824,879.03 ላይ በ2010 የተከፈለ ብር 1,468,175.50 ሲሆን እየተጣራ ያለ ሂሳብ ብር 356,699.59 መሆኑን፣
- 5004
  - **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** ሰኔ 2009 በ5004 በጀት ኮድ ላይ የታየው ብር 676,636.03 ሲሆን በ2010 በጀት ዓመት ሙሉ በሙሉ መከፈሉን፣
- 5028
  - **በጤና ሳይንስ ኮሌጅ** ከታየው ብር 40,031.59 የሪፈራል ሆስፒታል እና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሲለያዩ የቀረ የቦንድ ብር ሲሆን በሪፈራል ሆስፒታል ቦንድ እየተሰራ ስሆነ በ2010 በጀት ዓመት ዕልባት የሚያገኝ መሆኑን፣
  - **በቴክኖጂ ኢንስቲትዩት** ሰኔ 2009 በ5028 በጀት ኮድ ላይ የሚታይ ብር 12,333.00 እና በሪፈራል ሆስፒታል ብር 7,098.08 እየተጣሩ በ2010 በጀት ዓመት ዕልባት የሚያገኙ ሂሳቦች መሆናቸውን፣

- 5035
    - ሰኔ 2009 በ 5035 በጀት ኮድ ላይ የሚታየው ብር 94,186.38 ለሰራተኞች የተሰጠ የረዥም ጊዜ ብድር ሲሆን በሥራ ላይ ከተገኙ ሠራተኞች ላይ ብር 12,383.71 የተሰበሰበ ሲሆን ቀሪውንም ከኮሌጆች ጋር በመጻጻፍ እንዲቆረጥ እየተደረገ እንደሚገኝ፣

**የዉስጥ ገቢ ተከፋይ ሂሳብ**

- 5002
    - **በዋናው ግቢ** በሰኔ ወር ብር 512,971.38 በሰኔ ወር መጨረሻ ላይ የተሰበሰበ የሥራ ግብር ሲሆን በ2010 ለገቢዎችና ጉምሩክ ተከፈለ መሆኑን፣
    - **በቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩት** በሰኔ ወር ብር 643,360.48 የሚታይ ሲሆን ብር 453,814.98 በ2010 በጀት ዓመት የተከፈለ ሲሆን ቀሪው ብር 189,545.50 እየተጣራ ያለ ሒሳብ መሆኑን፣
    - **በሪፈራል ሆስፒታል** በሰኔ 2009 የሚታይ ብር149,776.82 ሲሆን የፕሮጀክቶችና የ CDC ከጤና ቢሮ ለእናቶች ጥምረትና ለሌሎች ክፍያዎች የመጣ ስለነበር በ2010 መከፈሉን፣
    - **በወንዶ ገነት ኮሌጅ** በሰኔ 2009 ብር 5,413,651.25 የሚታይ ሲሆን ጉዳዩም የፕጀክት ሂሳብ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ጋር ተቀላቅሎ ተመዝግቦ በተከፋይ የተያዘ ሲሆን በማኔጅመንት እየታየ ያለ እና ሂሳቡን ለይቶ ለመመዝገብ ለብቻ አካውንት ለመክፈት በሂደት ላይ ያለ መሆኑን፣

በአጠቃላይ በዩኒቨርሲቲው ሰኔ 2009 በ5002 በጀት ኮድ ከታየው ብር 6,716,124.98 ላይ በ2010 የተከፈለው ብር 1,128,939.90 ሲሆን እየተጣራ ያለ ሂሳብ ብር 5,587,185.08 መሆኑን፣

በምላሻቸው ገልጿል፡፡

## 6. <u>በጀት</u>

### 6.1 <u>ግኝት</u>፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ በዚህ መሠረት የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና

አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የዩኒቨርሲቲው የበጀት ሂሳብ ሲመዛዘን በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ከ10% በላይ ብር **10,000,613.49 መደበኛ በጀት 2,000,000.00 ካፒታል በጀት 12,000,613.49** ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ (የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቁጥር 20 ተመልክቷል፡፡)

6.2 <u>ስጋት</u> ፣

የወጪ በጀቱ በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

6.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውን የተጣጣመ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ በ2009 በጀት ዓመት አጠቃቀም በስራ ላይ ያልዋለ በጀትን በተመለከተ፣

- **በዋናው ግቢ ፡-**
  - በበጀት ዓመቱ ለዩኒቨርሲቲዉ የተመደበዉን በጀት በየሂሳብ ኮዳቸዉ ተጠይቆ የሚቀርብ ሲሆን የወጪ ሂሳብ አያያዙ ግን ከሚቀርበዉ የክፍያ ጥያቄ በመነሳት ቀጥታ በወጪ ሂሳብ መደቦች ላይ ከሚመዘገቡት በተጨማሪ ለምምርምርና ለመሳሰሉት በቅድሚያ ክፍያ የተያዙ ማለትም ተሰብሳቢ የሂሳብ ኮዶች ላይ ተመዝግበዉ ክፍያቸዉ የተፈጸሙ በርካታ በመሆናቸው በወጪ ሂሳብ መደብ ኮዶች (6000) ተመዝግቦ የማይታዩ በመሆኑ ከተመደበዉ በጀት ጋር ሲነጻጻር አጠቃቀሙን ከበጀት በታች ሊያደርገዉ መቻሉን፣
  - በተጨማሪም በሰኔ ወር ለተሰጡ አገልግሎች የክፍያ ጥያቄ ያልቀረበባቸዉ የወጪ የሂሳብ ርዕሶች ወይም የአገልግሎት ክፍያ (ቢል) በቀጣዩ በጀት ዓመት ሀምሌ ወር የሚቀርብ በመሆኑና ያልተከፈለ ስለሆነ በዓመቱ የበጀት አጠቃቀም ስራ ላይ ያልዋለ ሆኖ እንዲታይ አስተዋጽኦ ማድረጉን፣

በላከው ምላሽ ገልጿል፡፡

7. <u>ንብረት</u>፣

7.1 <u>የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ</u>፣

7.1.1 <u>ግኝት</u>፣

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ንዑስ 5 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግሥት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፤ የመጠቀም፤ የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ ሲያበቃ ወይም አገልግሎት ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ ማድረግ የሚል ሲሆን በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፤

<u>የአላቂ እና የቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ</u>፣

<u>**ዋናው ግቢ**</u>፣

**የዋናው ግቢ የአላቂ እቃ ንብረት ክፍልን በተመለከተ፡-**

- ብዛቱ 5,612 እሽግ የሚሆን አዳዲስ ለማስተማሪያነት የተገዙ ጠመኔዎች ከሁለት ዓመት በላይ ያለጥቅም በንብረቱ ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፤

**የዋናው ግቢ የምግብ ቤት ንብረት ክፍልን በተመለከተ፡-**

- በጁኒየር ተማሪዎች መመገቢያ ሚኒ ስቶር ውስጥ የምግብ ጥሬ እቃዎች ማለትም ጥቅል ጎመን፤ ድንች፤ ሽንኩርት፤ ካሮት የመሳሰሉት አትክልቶች ለአቀማመጥ ምቹ ባልሆነ ወይም ከመሬት ከፍታ በሌለው ሁኔታ መሬት ላይ የተቀመጡ መሆኑ፣

**የዋናው ግቢ ተመላሽ ንብረት ክፍልን በተመለከተ፡-**

- በተመላሽ ንብረት ክፍል ውስጥ በ2005 በጀት ዓመት ተመላሽ የሆኑ ብዛት 35 ዴል ኮምፒውተር፣ በ2006 በጀት ዓመት ተመላሽ የሆኑ ብዛት 84 ኤች ፒ ኮምፒውተር፣ ብዛት 179 አሰር ኮምፒውተር እንዲሁም ብዛት 162 ዴል ኮምፒውተር ተጠግነው አግልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ በባለሙያ ሳይረጋገጡ ወይም ሳይለዩ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣

**የዋና ግቢ የመድሃኒት አያያዝን በተመለከተ**

- የአገልግሎት ጊዚያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች/የተበላሹ መድኃኒቶች/ 109 አይነት የተለዩ መድሃኒቶች ከ2002-2008 በጀት ዓመት ጀምሮ በተለያየ ጊዜ የገቡ መድሃኒቶች በአንድ መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

- ከዋናው የመድኃኒት ስቶር የወጣው መድኃኒት እና በፕሪስክሪፕሽን ወረቀት ላይ የተመዘገበው መድኃኒት ከወጪ ቀሪ መከታተያ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ ተገናዝቦ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣
- በቴክኖሎጂ ኢንስቲተዩት ተማሪዎች ምግብ አዳራሽ ተጠናቆ ርክክብ ተፈጽሞ የካቲት /2009 ዓ.ም ስራ መጀመሩ በክፍሉ ሰራተኞች የተገለጸ ቢሆንም የክፍሉ ጣሪያው የሚያፈስ እና ኮርኒሱ ያልተስተካከለ መሆኑ፣

በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

7.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡
- በአሮጌ ዕቃዎች ላይ ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰድ ከፍተኛ መጠን ያለው የተለያዩ ንብረቶች ለበለጠ ብልሽት እንዲዳረጉ የሚያደርግ አሰራር ነው፡፡
- በህክምና መድኃኒቶች ላይ አስተማማኝ የቁጥጥር ስርዓት ካልተዘረጋ መድሃኒቶች ለታቀደው ዓላማ ላይውሉ ይችላሉ፡፡

7.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

- ለንብረት አስተዳደር ቁጥጥር እንዲመች በንብረት አስተዳደር መመሪያው ላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ የስቶክ መዛግብቶችን በመጠቀም አስፈላጊውን ምዝገባ ሙሉ በሙሉ በማድረግ የንብረቶችን ከወጪ ቀሪ በትክክል ማመሳከር እንዲሁም በመንግሥት ላይ ተጨማሪ ወጪ እንዳያስከትል በታዩት ግድፈቶች ላይ የእርምት እርምጃ ጊዜ ሳይሰጠው ሊወሰድ ይገባል፡፡
- በተጨማሪም በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት እቃዎች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተገቢው የሆነ እርምጃ ጊዜ ሳይሰጠው ሊወሰድ ይገባል፡፡

7.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የምግብ ቤት ንብረት ክፍል እና የመድሃኒት አያያዝን በተመለከተ ምላሽ ያልሰጠ ሲሆን፣

- ካለፉት አምስት አመታት ወዲህ አብዛኛው የትምህርት አሰጣጥ በኤል ሲ ዲ ፕሮጀክተር የሚፈጸም በመሆኑ ከዚያ በፊት የተገዙ ንብረቶች በመጋዘን ሊገኙ መቻላቸውን፣ ይሁን እንጂ ጠመኔ በባህሪው እርጥበት እስካልነካው ድረስ በአጭር ጊዜ የሚበላሽ ባለመሆኑ ለሌሎች የመንግስት ትምህርት ቤቶች

በንብረት ማዛወሪያ በማስተላለፍ ማስወገድ የሚቻል ቢሆንም ሂሳብ ነክ ትምህርቶች ጠመኔ ስለሚጠቀሙ በአዲስ መልክ ግዢ ከመፈጸም ይልቅ ይህንኑ ማቆየታቸውን፣

- የኤክትሮኒክስ እቃዎች ከሆኑት ውስጥ ኮምፒውተር አብዛኛው ጊዜ ያለፈባቸው፣ ነገር ግን የሚሰሩ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ግን ከዚህ ቀደም መለዋወጫቸው ለጥገና የዋሉ መሆናቸውን፣ የአወጋገድ ስርዓቱም በፌደራል ንብረት ግዢና ማስወገድ አገልግሎት በኩል ለኢንፎርሜሽን ኮሚውኒኬሽን ሚኒስቴር እንዲያስረክቡ ታዞ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቦታ ስለሌለው ለመረከብ ዝግጁ ባለመሆኑ በዩኒቨርሲቲው መጋዘን ተከማችቶ ሊገኝ መቻሉን፣

በምላሹ ገልጿል፡፡

8. <u>ልዩ ልዩ</u>፣

8.1 የ<u>ስጋት ተጋላጭነት መመሪያን በተመለከተ</u>፣

8.1.1 <u>ግኝት</u> ፣

የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ኃላፊነት የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 አንቀፅ 5 የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የመስሪያ ቤታቸውን ተልዕኮ ለማሳካት ስራዎች ውጤታማ የሆነ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት የመዘርጋት ኃላፊነት እንዳለባቸው እና ክፍል ሁለት ንዑስ አንቀፅ 5 ላይ የሥራ አመራሩ በስጋት ተጋላጭነት ላይ ተገቢና ተስማሚ እርምጃ መውሰድ እንዲችል በመስሪያ ቤቱ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ላይ የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ በየጊዜው መደረግ እንዳለበት እና አንቀፅ 06 የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች አፈፃፀም ስር የመንግስት መ/ቤቶች የውስጥ ቁጥጥር ዝርዝር የአፈፃፀም ስርዓትና የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች ማንዋል በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው መመሪያው ይገልፃል፡፡ በዚህም መሰረት ሲጣራ፣

- ዩኒቨርሲቲው ለተልዕኮው መሳካት ከሚያከናውናቸው ቁልፍ ተግባሮች ላይ በመመርኮዝ እና በሚያከናውናቸው የዕለት ከዕለት ሥራዎች ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶችን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚረዱ የአሰራር ስልቶችን በመቀየስ የዩኒቨርሲቲውን የስጋት ተጋላጭነት አስተዳደር ዕቅድ /Risk Management Plan/ ያልተዘጋጀ መሆኑና

- የውስጥ ቁጥጥር ዝርዝር የአፈፃፀም ስርዓትና የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች ማንዋል ለምሳሌ፡- ለግዥና ንብረት አስተዳደር የንብረት ስርጭት፣ ዕደላ፣ ርክክብ፣ ቁጥጥርና ለመሳሰሉት በህጉ መሰረት፣ ለሂሳብ ክፍል፣ ለፕሮጀክት ሂሳቦች /አስተዳደር፣ የክፍያ ስርዓት፣ በዩኒቨርሲተው ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ የአፈፃፀም ስርዓት እንዲኖረው/፣ ለተማሪዎች ምግብ ቤት፣ ለተሽከርካሪ ነዳጅ፣ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ማመንጫ ክፍሎች እና ለመሳሰሉት ተገቢ የሆነ ከመንግስት አዋጅ፣ ህግና ደንብ ጋር በማጣጣም ማንዋል መውጣት ሲኖርበት ያልወጣ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

8.1.2 <u>ስጋት</u>፣

ዩኒቨርሲቲው ለሚያከናውናቸው ተግባራት የስጋት ተጋለጭ የሆኑ ቦታዎችን በመለየት ተስማሚ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ካልዘረጋ እና በየጊዜው የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ የማያደርግ ከሆነ በዩኒቨርሲቲው የመልካም አስተዳደር ግንባታ፣ ፍትሃዊነት እና ግልፀኝነት ላይኖር እና የመንግስት ንብረትና ገንዘብ ለብልሹ አሰራር ሊጋለጥ ይችላል፡፡

8.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

ዩኒቨርሲቲው ለተልዕኮው መሳካት በሚያከናውናቸው ቁልፍ ተግባሮች ላይ በመመርኮዝ እና በሚያከናውናቸው የዕለት ከዕለት ሥራዎች ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶችን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚረዱ የአሰራር ስልቶችን በመቀየስ የስጋት ተጋላጭነት አስተዳደር ዕቅድ እና የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች ማንዋል /መመሪያ/፣ ለምሳሌ የፋይናንስ የውስጥ መመሪያ፣ የግዥና ንብረት የውስጥ መመሪያ፣ የምግብ ቤት የውስጥ መመሪያ፣ የፕሮጀክት ሂሳቦች የውስጥ መመሪያ እና ለመሳሰሉት የስራ ክፍሎች..ሊኖር ይገባል፡፡

8.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>፣

የሥራ አመራሩ በላከው መምላሽ በአስተያየቱ መሠረት አዘጋጅተን በ2010 ዓ.ም ተግባራዊ እናደርጋለን ብሏል፡፡

8.2 <u>በባንክ ስለሚከፈል የሰራተኞች ደመወዝን በተመለከተ</u>

8.2.1 <u>ግኝት</u>፣

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ዓ.ም አንቀጽ 12/3 ባንኩ የሰራተኞችን የተጣራ ደመወዝ ወደ ሰራተኞች የቁጠባ ሂሳብ ካስተላለፈ በኃላ ከመ/ቤቱ ተዘጋጅተቶ የተላከለትን የሰራተኛውን ስም፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥርና

የሚተላለፈውን የገንዘብ መጠን  የያዘ ሰነድ ላይ የሚመለከተው ሃላፊ ፈርሞበት  ክብ ማህተም በማድረግ አንድ ኮፒ መልሶ እንዲልክለት ከተደረገ በኃላ መስሪያቤቱ ከባንክ በሚደርሰው የዴቢትና የክሬዲት አድቫይስ መሰረት ለወጪው አስፈላጊውን የሂሳብ ምዝገባ እንደሚያከናውን ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው የየወሩ የተጣራ የሰራተኞች ደመወዝ በባንክ በኩል በሚከፈልበት ወቅት የሰራተኞች ስም፤ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እና የወሩ የተጣራ የደመወዝ መጠን የያዘ ዝርዝር በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ ክፍያ ወደሚፈፅመው ባንክ መተላለፍና ክፍያውም ከተፈፀመ በኂላ ባንኩ የሰራተኞቹን ስም ዝርዝር የያዘውን ሰነድ ላይ በሚመለከተው ኃላፊ ተፈርሞና ክብ ማህተም ተደርጎበት አንድ ኮፒ መልሶ ለተቋሙ መላክ ሲገባው፤ ከባንኩ ማረጋጋጫ ሳይቀርብ በቀጥታ በባንክ ዴቢትና ክሬዲት አድቫይስ ብቻ የተጣራ የሰራተኞች ደመወዝ ክፍያ  የሂሳብ ምዝገባ የተከናወነ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

8.2.2 <u>ስጋት</u>፣

የየወሩ የተጣራ የሰራተኞች ደመወዝ ሰነድ  ኮፒ ባንኩ ያረጋገጠውን  ቀሪውን ማስረጃ አለመያዝ አግባብ ላልሆነ ሠራተኛ የደመወዝ ክፍያ እንዲፈጸም መንገድ ከመክፈቱም በተጨማሪ የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

8.2.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

በየወሩ በባንኩ የተረጋገጠ ደመወዝና ተያያዥ ክፍያዎች የተፈፀመበት ዝርዝር ኮፒ ከቀረበ በኃላ ተገቢውን የሂሳብ ምዝገባ ሊደረግ ይገባል፡፡

8.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የኦዲት አስተያየት ከተሰጠ ጊዜ ጀምሮ በቀሪው ወደ ባንክ የሚላከው የደሞዝ ዝርዝር ባንኩ ስለመቀበሉ ማኅተም በማድረግ ተግባራዊ እያደረገ እንደሚገኝ በምላሹ ገልጿል፡፡

8.2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

አስቀድሞ ዝርዝሩን አስፈርሞ መስጠት ብቻ ሳይሆን ለደመወዝ  የወጪ ምዝገባ ክፍያው የተፈጸመበት ዝርዝር በባንኩ የሚመለከተው ሃላፊ ተፈርሞበትና ማህተም ተደርጎበት ከባንኩ መወሰድ እንዳለበት መመሪያው ስለሚያዝ ለወደፊቱ በዚሁ መሠረት ሊፈጸም ይገባል፡፡

9. <u>በ2008 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶችን በተመለከተ፤</u>

9.1 <u>ግኝት፣</u>

የፌደራል መንግሥት የፋይናስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 አንቀጽ 10 ለ እና ሐ ሂሳብ ኦዲት ማስደረግ በሚለዉ ሥር በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሰረት በወቅቱ የእርምት እርምጃን የመዉሰድ፣ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊና የኦዲት ሪፖርት ላቀረበዉ አካል የማሳወቅ ኃላፊነት እንዳለበት መመሪያዉ ቢያመለክትም የማስተካከያ እርምጃ ሳይወሰድባቸዉ የተገኙ ግኝቶች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

<u>የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት፣</u>

- የዩኒቨርሲቲው መምህር ለሆኑት አንድ ፕሮፌሰር የሁለት ምሁራንን የምርምር ሥራ ለገመገሙበት ብር 3,000.00 ክፍያ ሲፈፀም የተቆረጠው ብር 1,615.39፤ እንዲሁም ከሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የኤም.ፒ.ኤች ተማሪዎችን ላማከሩና ለፈተኑ መምህራን ከተፈፀመው ጠቅላላ ክፍያ ብር 47,600.00 ላይ የተቀነሰው ስራ ግብር ብር 15,960.00፤ በድምሩ ብር 17,575.39 የስራ ግብር ከተጠቃሚዎቹ መቀነስ ሲገባው አለአግባብ ከውስጥ ገቢ በመሸፈን ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ በህክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ ከሪፈራል ሆስፒታል በአዋዳ ቢዝነስ ኮሌጅ በተመረጡ ናሙናዎች ለተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ለፋሲሊቲ ሠራተኞች፤ ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ፤ ለዲሲፒሊን ኮሚቴ አባላት፤ ለተማሪዎች ዲሲፒሊን ኮሚቴ አባላት፤ ለፒፒኤም ኮሚቴ አባላት፤ ለሆስፒታል ማናጀርና ለፕላን ኤክስፐርት፤ ለMPH ሠራተኞች፤ ለቢፒአር ካሚቴ ለሥልጠና ማዕከል አስተባባሪ በሚል ለፐሮፎርማ ከፋች፣ ለረዳት ሪጅስራሮች እና ለዳታ አናሊስቶች የማበረታቻ ክፍያ፤ በጠቅላላው ብር 1,689,890.96 ያላግባብ የተከፈለ መሆኑ፤

<u>የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት፣</u>

**የወጪ ሂሳብ፣**

ዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ካውንስል የተለያዩ ውሳኔዎችን በመስጠት ከተፈጸሙ ክፍያዎች ውስጥ፡-

- ዩኒቨርስቲው በሥራ አመራሩ ውሳኔ የክረምት የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች ለመፈተን የመጡ መምህራን ለዋና አማካሪዎች (ለአድቫይዘር) በዋና ግቢ ብር **851,570.00**፣ በጤና ሳይንስ እና ሪፈራል ሆስፒታል ብር 84,000.00 ተከፍሎ መገኘቱ፣
- በዋና ግቢ ብር 508,091.00 ለመምህራን ከተከፈለው የትርፍ ሰዓት ክፍያ የሥራ ግብር መቀነስ ቢኖርበትም ዩኒቨርስቲው በራሱ ብር 169,941.00 ታክስ ሸፍኖ መገኘቱ እና በአጠቃላይ ብር **1,105,511.00** ደንብና መመሪያ ሳይኖረው ከፍሎ መገኘቱ፡
- በአካዳሚክ የትምህርት ጥራት ለተሳተፉ በሚል በዋና ግቢ ብር 150,250.00፣ በቴክኖሎጂ ኮሌጅ ብር 133,566.00 እና በግብርና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 161,806.00፣ በድምሩ ብር 445,622.00 የማበረታቻ በሚል ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ዩኒቨርስቲው የኮሌጅ ኃላፊዎች ውስጥ ለሚገኙ የአስተዳደር ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ፈቃድ ሳይገኝ የቤት አበል በጤና ሳይንስ እና ሪፈራል ሆስፒታል ብር **53,601.75 እና** በወንዶ ገነት ኮሌጅ ብር 15,300.00፣ በድምሩ ብር **68,901.75** የቤት አበል ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ብር 5,329,915.35 በሥራ አመራር ካውንስል ውል ፈታኞችና የአማካሪዎች፣ የማበረታቻና የአስተባባሪነት፣ ለአሰተዳደር ሠራተኞች የቤት አበል፣ ለስፔሻልስት ሀኪሞች እና ለጠቅላላ ሀኪሞች፣ ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ድጋፍ በሚል ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ መገኘቱ፣

**የውስጥ ገቢ ሂሳብ፣**

- የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ የአከፋፈል ሥርዓትን በተመለከተ በብልጫ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር **288,792.00** መኖሩ፣
- በሥራ አመራር ውሳኔ የዋና እና ረዳት አማካሪዎች፣ ለውስጥና ለውጭ ፈታኞች ማበረታቻ በሚል ብር **1,022,171.11** መከፈሉ፣
- ተገቢው የክፍያ ተመን/ሬት/ ዝርዝር ማሰረጃ ሳይቀርብ የተከፈለ ብር **2,009,690.70** ሲሆን፣ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ከመምህራን ከሚከፈላቸው መቀነስ የነበረበት የሥራ ግብር ብር **237,596.85** በዩኒቨርሰቲው ተሸፍኖ መገኘቱ፣

**ተሰብሳቢ ሂሳብ**

- በ4202 ሂሳብ መደብ በጥሬ ገንዘብ ጉድለት በአቶ መስፍን ደሴ ስም በተቀጽላ ሌጀር ቁጥር 10 ብር 38,380.94 ያልተሰበሰበና ምንም እቅስቃሴ ሳይደረግበት አሁንም በተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፡-

<u>የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት</u>፣

- በኃላፊነት ላይ ላሉ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ ለቴክኒክ አሲስታንት ኢንስቲትዩት አለአግባብ የተከፈለ የቤት አበል እና ጥቅማ ጥቅም ብር 1,622,360.46 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- በክረምት ዲፕሎማ መረሀ ግብር ለተሳተፉ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች አላግባብ የተከፈለ ብር 1,089,675.30 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- ለሐዋሳ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ለዩኒቨርስቲው መኖሪያ ቤት የውል ቁጥር 416 የተከፈለው ብር 41,548.05 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- በመደበኛ የሥራ ሰዓት የንብረት ቆጠራ ያደረጉ፣ በተማሪዎች የምረቃ በዓል ያለአግባብ የውሎ አበል የተከፈለ ብር 188,343.00 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- ብር 203,978.08 ለዲስፒሊን ኮሚቴ፣ ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ፣ የጥራት እና የቁጥጥር ኮሚቴ እና ሌሎች በሥራ አመራር ውሳኔ የተከፈለ ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- ከወንዶ ገነት የተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ሲከፈል መቀነስ ያለበት ታክስ ብር 132,700.00 በኮሌጅ የተሸፈነው ሂሳብ ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- በአስተዳደር ሠራተኞች ላሉ የተለያዩ ክፍሎች ያለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 101,867.05 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- የኢፊድሪ ት/ት ሚኒስቴር ካወጣ የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ውጭ ተከፍሎ የተገኘ ብር 374,860.00 ተመላሽ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣
- ብር 5,116,841.79 ከተለያዩ ድርጅቶች መሰብሰብ ያለበት ቅጣት ወደ ገ/ኢ/ል/ሚ ፈሰስ ሊደረግ ሲገባ አለመደረጉ፣

8.4.2 <u>ስጋት</u> ፣

በኦዲት ሪፖርቱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት የእርምት እርምጃ አለመወሰዱ ለመንግሥት ሀብት ብክነት መንገድ የሚከፍት ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡

8.4.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲቀረፉና ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በኦዲት በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ የበኩሉን አስተዋፅኦ መወጣት እንደሚገባው በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

8.4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

<u>የ2008 በጀት ዓመት</u>

- **በዋናው ግቢ፡-** የሥራ ግብር ከውስጥ ገቢ መሸፈን ቀደም ባሉት ዓመታት ከመማር ማስተማር ጋር የሚፈጸሙ ክፍያዎች ሲከናወኑ የነበረበት አግባብ የሥራ ግብሩ ተቀንሶ ቀሪው መጠን ለተከፋዮች የሚደርስ፣ የሥራ ግብሩም ለመንግስት እንደሚከፈል፣ ከተገለጸው የኦዲት አስተያየት በኋላ ግን ይህ የሥራ ግብር ከተከፋዩ ላይ ሲቀነስ በግልጽ እንዲታይ በሚያደርግ አሰራር መተካቱን፣ በሁለቱም መንገዶች ለተከፋዩ የሚደርሰው የገንዘብ መጠንና ለመንግስት የሚከፈለው የሥራ ግብር ግን ተመሳሳይ መሆናቸውን፣
- ለኮሚቴ የሚከፈሉ ክፍያዎች ከኦዲት አስተያየት በኋላ የቆሙ መሆኑን፣

<u>የ2007 በጀት ዓመት</u>

- **በዋናው ግቢ፡-**
  - የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ላማከሩና ለፈተኑ የተፈጸመ ክፍያ ከመማር ማስተማር ሥራዎች በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው የድህረ ምረቃ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፍና የምርምር ሥራ ሲያከናውኑ ላማከሩ መምህራን እንዲሁም ደግሞ ተማሪዎች የምርምር ሥራቸውን በግልጽ በሚያቀርቡበት ወቅት ለሚፈትኑ የውስጥና የውጪ ፈታኞች በዩኒቨርሲቲው ክፍያ እንደሚፈጸም፣ ይህም ክፍያ ከተጠቀሰው የኦዲት ማስታወሻ በኋላ የሚፈጸመው ቀደም ሲል እንደነበረው በጥቅሉ ሳይሆን ፈታኞቹ ከላይ የተጠቀሰውን ሥራ ሲያከናውኑ ሊኖር የሚችለውን የሥራ ጫና ወደ LEH (Lecture equivalent hour)

በመቀየርና እንደፈታኞቹ የአካዳሚክ ማእረግ በተቀመጠው የክፍያ "Rate" ተባዝቶ በሚከናወን የአሰራር አግባብ መተካቱን፣

- በተመሳሳይም በዩኒቨርሲቲው በሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በሕክምና ትምህርት ቤት የሚገኙ ሀኪሞች በትምህርት ክፍል ውስጥ የማስተማር እንዲሁም ደግሞ በሆስፒታሉ ውስጥ የህክምና ሥራ የሚያከናውኑ መሆናቸውን፣ ለነዚህም ሀኪሞች የሚከፈለው ክፍያ ከላይ ከተቀመጠው የአካዳሚክ ጭነት በተጨማሪ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለሀኪሞቹ እንዲከፈል በአስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የተከናወነ መሆኑን፣
- በአቶ መስፍን ደሴ በጥሬ ገንዘብ በጉድለት የሚታየው መጠን ዩኒቨርሲቲው ወደ ሕግ ያቀረበውና በሕግም የተያዘ ጉዳይ መሆኑን፣

<u>የ2006 በጀት ዓመት</u>

**በዋናው ግቢ፡-**

- በክረምት ወቅት የተከናወነው የዲፕሎማ ፕሮግራም ባለቤቱ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሳይሆን በክልሉ በሀዋሣ ከተማ የሚገኘው የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ መሆኑን፣ ባለቤት የሆነው ኮሌጅ ከዩኒቨርሲቲው ጋር ባደረገው ስምምነት የኮሌጁን ተማሪዎች በአደራ ተቀብሎ በኮሌጁ "Curriculum"መሠረት ያስተማረ ሲሆን፤ ክፍያዎቹም በዚሁ ስምምነት መሠረት የተከናወኑ መሆናቸውን እና የሥራውም ሙሉ ሰነድ የሚገኘው በባለቤቱ በኮሌጁ እጅ መሆኑን፣

በተጨማሪም ይኸው ሥራ በ2007 ዓ/ም የተከናወነ ሲሆን በኦዲት ግኝት ግን የተያዘ አለመሆኑን፣

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን (ERA) በመንገድና ተዛማጅ ሥራዎች ላይ በአገራችን የተሰማሩ ባለሙያዎችን ብዛትና የብቃት ደረጃ ለማሳደግ በያዘው ፕሮግራም መሠረት በዩኒቨርሲቲው ከሚገኙ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶች ጋር ስምምነት ላይ መድረሳቸውን እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በመማር ማስተማሩ ላይ ለሚሳተፉ መምህራን ክፍያ የሚከናወነው በፕሮጀክቱ ስምምነት ላይ በተቀመጠው "Rate" መሠረትና ለፕሮጀክቱ ከERA ከሚላክ ገንዘብ ሲሆን ከዚህ ውጪ ላሉ የመማር ማስተማር ሥራዎች ግን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ትምህርት ሚኒስቴር በወጣ የክፍያ "Rate" መሠረት መሆኑን፣

- በሀዋሣ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ከዩኒቨርሲቲው የተከፈለው በመኖሪያ ቤት የሚኖሩ ግለሰቦች እንዲከፍሉ ደብዳቤ ተጽፎ በክትትል ላይ እንደሚገኝ፣

- አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 188,343.00፣ ለተለያዩ ኮሚቴዎች የተከፈለ ብር ብር 203,978.08፣ አለ አግባብ የተከፈለ ጥቅማ ጥቅም ብር 132,700.00፣ አለ አግባብ የተከፈለ ትርፍ ሠዓት ብር 101,867.05 ለየኮሌጆቹ ደብዳቤ ተፅፎ የተከፈላቸው ግለሰቦች ተመላሽ እንዲያደርጉ በክትትል ላይ መሆኑን፣
- የጉዳት ካሳን በተመለከተ ከኦዲት አስተያየቱ በኋላ በትክክል መሰብሰብ ያለበት የጉዳት ካሳ እየተሰበሰበ መሆኑን፣

### 8.4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በእኛ በኩል አሁንም ቢሆን፣

- ያለአግባብ የተፈጸሙና ተመላሽ መደረግ ያለባቸው ክፍያዎች ተመለሽ እንዲደረጉ፣
- ማስረጃ ሊቀርብላቸው ለሚገባ እንዲቀርብ እና
- ሌሎች መስተካከል ያለባቸው አሰራሮች እንዲስተካከሉ

እናሳስባለን፡፡

**በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡**

## <u>አባሪ 1 ከተገኘው ጥቅም ላይ ያልተቀነሰ ስራ ግብር፣</u>

| ተ.ቁ | ቀን | የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር | ወጪዉን ያዘዉ ባለሥልጣን ስም | የተከፈለዉ | የወጪው ምክንያት | መቀነስ የነበረበት ስራ ግብር | ተቀነሶ የተገኘ ታክስ (2%) | በልዩነት ያልተቀነሰ ግብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 30/05/09 | Jv 790797 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | ለመምህር ሻንቆ ሰጎያ | የትርፍ ሰዓት የሠሩበት የሥራ ግብር መቆረጥ ሲገባዉ 2% | 1,630.20 | 124.8 | 1,506.30 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የተቆረጠ | | | |
| 2 | 30/08/09 | Jv 790794 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር አርባ አሻ | ‹‹ ›› | 1,326.50 | 83.20 | 1,243.30 |
| 3 | 30/08/09 | Jv 790794 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ሰለሞን | ‹‹ ›› | 910.30 | 83.20 | 827.10 |
| **4** | **30/08/09** | Jv 790794 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | **መምህር ዮሐንስ ደመቀ** | ‹‹ ›› | 1,569.50 | 124.80 | 1,444.70 |
| 5 | 30/08/09 | Jv 790794 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ሙሉቀን ሰዉነት | ‹‹ ›› | 4,062.30 | 249.60 | 3,812.70 |
| 6 | 30/08/09 | Jv 790794 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ሻንቆ ሰጎያ | ‹‹ ›› | 1,600 | 124.80 | 1,506.30 |
| 7 | 29/07/09 | BPV422229 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር መለስ ጫኔ | ‹‹ ›› | 7,818.50 | 448.00 | 7,370.50 |
| 8 | 03/02/09 | BPV422001 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር መክብብ ያዕቆብ | ‹‹ ›› | 6,534.50 | 380.80 | 6,153.70 |
| 9 | 17/02/09 | BPV421977 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ግርማ አወቀ | ‹‹ ›› | 2,078.50 | 120 | 1,958.50 |
| 10 | 20/10/09 | Jv 794173 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ታሪኩ በለጠ | ‹‹ ›› | 908.28 | 117.86 | 790.42 |
| 11 | 20/10/09 | Jv 794173 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር አምደወርቅ ጥላሁን | ‹‹ ›› | 3595.78 | 291.19 | 3,304.59 |
| 12 | 20/10/09 | Jv 794173 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ብሩክ ቡሴር | ‹‹ ›› | 7,842.26 | 533.84 | 7,308.42 |
| 13 | 20/10/09 | Jv 794173 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ተመስገን አኔቦ | ‹‹ ›› | 1,301.56 | 149.32 | 1,152.24 |
| 14 | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ኢያሱ ማርቆስ | ‹‹ ›› | 2,543.44 | 180.26 | 2,363.18 |
| 15 | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ወ/ማሪያም በዛብህ | ‹‹ ›› | 6,898.91 | 416.01 | 6,482.90 |
| 16 | 16/09/ | Jv | አቶ አሰፋ | መምህር ፍሬህይወት ፀጋዬ | ‹‹ ›› | 1,155.30 | 90.13 | 1,065.17 |
| 17 | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ዳዊት ሀ/የሱስ | ‹‹ ›› | 2,543.44 | 180.26 | 2,363.18 |
| 18 | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ቸርነት ወገኔ | ‹‹ ›› | 752.59 | 221.86 | 3,530.73 |
| 19 | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ተስፋዬ አዱኛ | ‹‹ ›› | 4,831.91 | 277.34 | 4,554.57 |
| 20 | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ሳሙኤል በላይነህ | ‹‹ ›› | 4,831.91 | 277.34 | 4,554.57 |
| 21 | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ዮሐንስ ኃይል | ‹‹ ›› | 4,831.91 | 277.34 | 4,554.57 |
| 22 | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ማርቆስ ማዴቦ | ‹‹ ›› | 4,831.91 | 277.34 | 4,554.57 |
| 23 | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ጥላሁን ተድላ | ‹‹ ›› | 4,831.91 | 277.34 | 4,554.57 |
| 24 | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር ደምመላሽ መረሻ | ‹‹ ›› | 2,278.50 | 138.67 | 2,139.83 |
| | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር መንግሥተአብ ገ/የሱስ | ‹‹ ›› | 2,965.20 | 170.67 | 2,794.53 |
| | 16/09/09 | Jv 790819 | አቶ አሰፋ ዮሐንስ | መምህር አስማረ መህረት | ‹‹ ›› | 4,831.91 | 277.34 | 4,554.57 |
| | | | | | | | **ድምር** | **86,445.71** |

<u>አባሪ 2 </u>እንግዳ መምህራን <u>ከተገኘው ጥቅም ላይ ያልተቀነሰ ስራ ግብር፣ </u>እንግዳ መምህራን payment for par time Guest lecturer ,trainer facilitator,external examiner

| ተ.ቁ | ቀን | የደረሰኝ አይነት | የደረሰኝ ቁጥር | የሂሳብ መደብ | የተከፈለበት ምክንያት | ግብር የሚከፈልበት ገቢ | መከፈል የነበረበት ታክስ | የተከፈለ 2% | በልዩነት ያልተቀነሰ ግብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 3/6/09 | BPV | 531039 | 6251 | 11/01/2008 እስከ 30/04/2008 | 480 ሰአት*120 ብር 57,600 | 57,600*35%=20,160 | ብር 1,152 | 19,008.00 |
| 2 | 26/5/09 | BPV | 531119 | 6116 | 26/04/2009 እስከ 25/05/2009 | 160ሰአት*120 ብር 19,200 | 19,200*35 ብር 6,720.00 | 384 | 6,336.00 |
| 3 | 17/06/2009 | BPV | 531104 | 6116 | 19/03/2009 እስከ 18/04/2009 | 160ሰአት*120ብር 19,200 | 19,200*35ብር 6,720.00 | 384 | 6,336.00 |
| 4 | 13/06/2009 | BPV | 531014 | 6251 | 15/052009 እስከ 15/06/2009 | 292ሰአት*120 በማሰብ ብር 35,040 | 35,040*35 ፐርሰት ብር 12,264.00 | 700.80 | 11,563.20 |
| 5 | 17/06/2009 | BPV | 531105 | 6116 | 26/03/2009 እስከ 25/04/2009 | 160ሰአት*120 በማሰብ ብር 19,200 | 19,200*35 ፐርሰት ብር 6,720.00 | 384 | 6,336.00 |
| 6 | 16/05/2009 | BPV | 531057 | 6251 | 17/04/2009 እስከ 19/05/2009 | 416.66ሰአት*120 በማሰብ ብር 50,000 | 50,000*35 ፐርሰት ብር 17,500 | 1000 | 16,500.00 |
| 7 | 12/05/2009 | BPV | 531011 | 6251 | 09/04/2009 እስከ 07/05/2009 | 292ሰአት*120 በማሰብ ብር 35,040 | 35,040*35 ፐርሰት ብር 12,264.00 | 700.80 | 11,563.20 |
| 8 | 04/08/2009 | BPV | 216716 | 6251 | 05/07/2009 እስከ 04/08/2009 | 500ሰአት*120 በማሰብ ብር 60,000 | 60,000*35 ፐርሰት ብር 21,000.00 | 1,200 | 19,800 |
| 9 | 03/08/2009 | BPV | 216709 | 6251 | 21/06/2009 እስከ 21/07/2009 | 417ሰአት*120 በማሰብ ብር 50,000 | 50,000*35 ፐርሰት ብር 17,500.00 | 1000 | 16,500.00 |
| 10 | 28/08/2009 | BPV | 216707 | 6116 | 01-30/07/2009 | 334ሰአት*120 በማሰብ ብር 40,080 | 40,080*35 ፐርሰት ብር 14,028.00 | 801.6 | 13,226.40 |
| 11 | 11/08/2009 | BPV | 216228 | 6116 | 30/06/2009 እስከ 30/07/2009 224ሰአት*120 በማሰብ ብር 26,880 የተከፈለ | | 26,880*35 ፐርሰት ብር 9,408.00 | 537.60 | 8,870.40 |
| 12 | 04/08/2009 | BPV | 216227 | 6116 | 30/06/2009 እስከ 30/07/2009 224ሰአት*120 በማሰብ ብር 26,880 የተከፈለ | | 50,000*35 ፐርሰት ብር 17,500.00 | 1000.00 | |
| 13 | 28/09/2009 | BPV | 217138 | 6251 | 21/08/2009 እስከ 21/09/2009 416.66ሰአት*120 በማሰብ ብር 40,080.00 የተከፈለ | | 40,080*35 ፐርሰት ብር 14,028.00 | 801.60 | |
| 14 | 04/08/2009 | BPV | 216226 | 6116 | 01-30/08/2009 334ሰአት*120 በማሰብ ብር 40,000 የተከፈለ | | 40,080*35 ፐርሰት ብር 14,000.00 | 800.00 | 13,200.0 |
| 15 | 25/12/08 | BPV | 68241 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ ነሃሴ 1-30/2008 ትሬኒንግ ለሰጡ በሚል ብር 35,040.00 | | (35,040*0.35) ብር 12,264.00 | 700.80 | **11,563.20** |
| 16 | 16/12/08 | BPV | 68232 | 6116 | በቀን 16/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 68232 በሂሳብ መደብ 6116 በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ 13/11/08- 13/12/08 ዓ.ም ስልጠና ለሰጡ በሚል ብር 35,040 | | (26,880 *0.35)=ብር 9,408.00 | 537.60 | 8,870.40 |
| 17 | 10/12/08 | BPV | 68230 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ 5/11/08 — 5/12/08 ዓ.ም ስልጠና ለሰጡ በሚል ብር 35,040.00 ክፍያ | | (35,040 *0.35)=ብር **12,264.00** | 700.80 | **11,563.20** |
| 18 | 5/12/08 | BPV | 68227 | 6116 | ከ 02/11/08 — 02/12/08 ስልጠና ለሰጡ በሚል ብር 35,040 | | 35,040*0.35)=ብር 12,264.00 | 700.8 | **11,563.20** |
| 19 | 5/12/08 | BPV | 68226 | 6116 | በቀን 5/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር | | 35,040*0.35)=ብር | 700.80 | 11,563.20 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 68226 በሂሳብ መደብከ2 July/2008 ስልጠና ለሰጡ በሚል ብር 35,040 ክፍያ ሲፈፀም | 12,264.00 | | |
| 20 | 02/12/08 | BPV | 68222 | 6116 | በቀን 2/12/08 68222 በሂሳብ መደብ 6116 በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ 5/10/08- 5/11/08 ስልጠና ለሰጡ በሚል ብር 26,880 ክፍያ ሲፈፀም | (26,880*0.35) ብር 9,408.00 | 537.6 | 8,870.40 |
| 21 | 2/12/08 | BPV | 68221 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ስልጠና ለሰጡበት በሚል ብር 28,800 | ( 28,800*0.35) ብር 10,080.00 | 576 | **9,504.00** |
| 22 | 29/11/08 | BPV | 68219 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከሃምሌ 1-30/2016 ስልጠና ለሰጡበት በሚል ብር 39,996 ክፍያ ሲፈፀም | (39,996*0.35)ብር 13,998.60 | 799.92 | **13,198.68** |
| 23 | 14/11/08 | BPV | 68207 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ስልጠና ለሰጡበት በሚል ብር 35,000 ክፍያ ሲፈፀም | (35,000*0.35)ብር 12,250.00 | 700 | 11,550.00 |
| 24 | 14/11/08 | BPV | 68206 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ገስት ሌክቸረር ስልጠና ለሰጡበት በሚል ብር 35,040 ክፍያ ሲፈፀም | (35,040*0.35)ብር 12,264.00 | 700.8 | 11,563.20 |
| 25 | 11/11/08 | BPV | 68205 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ገስት ሌክቸረር ስልጠና ለሰጡበት በሚል ብር 30,040.00ክፍያ ሲፈፀም | ( 35,040*0.35)ብር 10,514 | 600.8 | 9,913.20 |
| 26 | 06/11/08 | BPV | 68204 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ገስት ሌክቸረር ስልጠና ለሰጡበት በሚል ብር 35,040 ክፍያ ሲፈፀም | (35,040*0.35)ብር 12,264.00 | 700.8 | 11,563.20 |
| 27 | 19/04/09 | BPV | 0847809 | 6231 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ12/03/09- 12/04/09 ዓ.ም ስልጠና ለሰጡበት በሚል ብር 35,040 ክፍያ ሲፈፀም | (35,040*0.35)ብር 12,264.00 | 700.8 | **11,563.20** |
| 28 | 19/04/08 | BPV | 0847808 | 6116 | በቀን 19/04/09 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 0847808 በሂሳብ ደብ 6231 በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ ህዳር15/2009- ታህሳስ15/2009 ዓ.ም ስልጠና ለሰጡበት በሚል ብር 35,040 ክፍያ ሲፈፀም | (35,040*0.35 )ብር 12,264.00 | 700.80 | **11,563.20** |
| 29 | 28/11/08 | BPV | 084774 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለ3ኛ ዓመት ተማሪዎች Radiothepy እና Nuclear Medicine ያስተማሩ መምህራን ከ November 01/2016 — November 30/2016 ስልጠና የሰጡበት በሚል | (19,200*0.35) ብር 6,720 | 384 | 6,336.00 |
| 30 | 14/04/09 | BPV | 0847689 | 6251 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ 17/3/09- 16/4/09 ዓ.ም ስልጠና የሰጡ በሚል ብር 50,000 ክፍያ ሲፈፀም | (50,000*0.35) ብር17,500 | 1000 | 16,500.00 |
| 31 | 28/04/09 | BPV | 0847773 | 6251 | ➢ በቀን 28/04/09 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 0847773 | 19,200*0.35) ብር 6720.00 | 384 | 6,336.00 |
| 32 | 27/04/09 | BPV | 0847765 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ ሃምሌ 2008- እስከ ታህሳስ 2009 ስልጠና የሰጡበት በሚል ብር 28,800 ክፍያ ሲፈፀም | (28,800*0.35) ብር 10,080.00 | 576 | **9,504.00** |
| 33 | 21/07/09 | BPV | 216701 | 6251 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በካንሰር ህክምና ክፍል ከ March1- march 31/2017 ስልጠና ለሰጡበት በሚል ብር 35,000 ክፍያ ሲፈፀም | (35,000*0.35)ብር 12,250.00 | 700) | **11,550.00** |
| 34 | 21/07/09 | BPV | 216701 | 6251 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በካንሰር ህክምና ክፍል ከ March1- march 31/2017 ስልጠና ለሰጡበት በሚል ብር 35,000 ክፍያ ሲፈፀም | (35,000*0.35)ብር 12,250.00 | 700 | **11,550.00** |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 35 | 22/05/09 | BPV | 531018 | 6251 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ January1 ,2017-31,2017 ስልጠና የሰጡበት | (35,000*0.35)ብር 12,250.00 | 700 | 11,550.00 |
| 36 | 19/04/09 | BPV | 0847811 | 6251 | በቀን 19/04/09 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 0847811 በሂሳብ መደብ 6231 በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ 19/3/09- 21/04/09 ድረስ ትሬኒንግ የሰጡበት በሚል ብር 47,400 ክፍያ ሲፈፀም | (47,400*0.35) ብር **16,590.00** | 948 | **15,642.00** |
| | | | | | | ድምር | | **422,345.88** |
| | | | | | የወሰጥ ገቢ ሂሳብ | | | |
| 1 | 19/08/09 | BPV | 578039 | 6116 | ዩኒቨርሲቲው በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎችን ላስተማሩ መምህራን ከጫና በላይ/over lode payment/ የመጋቢት15 እሰከ ሚያዚያ15/2009 ወር ክፍያ ለ334 ሰዓት የስተማሩበት*በብር120 ብር40,080.00 ከተፈለው 40,080.00 ከገቢ ግብር ታክስ 35% ብር14,028.00 መቀረጥ ሲኖርበት 2% ብር 801.60 በመቆረጡ በልዩነት **ብር13,226.40** ሳይቆረጥ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በአጠቃላይ ድምር **መከፈል ከነበረው ገንዘብ በልዩነት የተከፈለ መሆኑ**፡፡በተጨማሪም መቆረጥ የነበረበት ግብር ብር በልዩነት ሳይቆረጥ ተገኝቷል፡፡ | | | **13,226.40** |
| 2 | 26/08/09 | BPV | 216475 | 6116 | ዩኒቨርሲቲው በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎችን ላስተማሩ መምህራን ከጫና በላይ/over lode payment/ የመጋቢት21 እሰከ ሚያዚያ21/2009 ወር ክፍያ ለ416.67 ሰዓት የስተማረበት*በብር120 ብር50,000.00 ከተፈለው ገንዘብ ከገቢ ግብር ታክስ 35%ብር17,500.00 መቀረጥ ሲኖርበት 2% ብር 1000.00 በመቆረጡ በልዩነት **ብር16,500.00** ሳይቆረጥ ተገኝቷል፡፡ | | | **16,500.00** |
| | | | | | ድምር | | | **29,726.40** |

**አባሪ 3**

| ተ.ቁ | ቀን | የደረሰኝ አይነት | የደረስኝ ቁጥር | ሂሳብ መደብ | የተከፈለበት ምክኒያት | ያልተቀረጠ ታክስ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 09/06/09 | BPV | 527101 | 6116 | ዩኒቨርሲቲው ሪፈራል ሆስፒታል school of Medical Department of surgery neurosurgery unit አገልግሎት ለሰጡበት **ብር 29,565.** ከተከፈለው ገንዘብ ላይ መቆረጥ ያለበት የገቢ ግብር (29,565.00*35%ብር 10,347.75 መቆረጥ ሲገባው ለሁለት ፐርሰንት 591.30 በልዩነት **ብር9,756.45** ሳይቆረጥ ተገኝቷል ፡ | **9,756.45** |
| 2 | 19/05/09 | BPV | 527102 | 6116 | በቀን 19/05/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 527102 በሂሳብ መደብ 6116 ዩኒቨርሲቲው ሪፈራል ሆስፒታል school of Medical Department of surgery neurosurgery unit አገልግሎት ለሰጡበት ብር 29,565.00 ከተከፈለው ገንዘብ ላይ መቆረጥ ያለበት የገቢ.ግብር(29,565.00*35%ብር 10,347.75 መቆረጥ ሲገባው ለሁለት ፐርሰንት 591.30 በልዩነት **ብር9,756.45** ሳይቆረጥ ተገኝቷል | **9,756.45** |
| 3 | 21/02/09 | BPV | 5276015 | 6116 | ዩኒቨርሲቲውሪፈራልሆስፒታል school of Medical Department of surgery orthopedics unit አገልግሎት ለሰጡበት ብር 33,671.25 ከተከፈለው ገንዘብ ላይ መቆረጥ ያለበት የገቢ ግብር (33,671.25*35%) ብር 11.784.94 መቆረጥ ሲገባው ለሁለት ፐርሰንት 673.42 በልዩነት **ብር**11.111.51 ሳይቆረጥ ተገኝቷል ፡፡ | 11,111.51 |
| 4 | 17/02/09 | BPV | 5276012 | 6116 | ዩኒቨርሲቲው ሪፈራል ሆስፒታል school of Medical Department of surgery orthopedics unit አገልግሎት ለሰጡበት ብር 33,671.2 ከተከፈለው ገንዘብ ላይ መቆረጥ ያለበት የገቢ ግብር (33,671.25*35%) ብር 11.784.94 መቆረጥ ሲገባው ለሁለት ፐርሰንት 673.425 በልዩነት **ብር ብር**11.111.51 ሳይቆረጥ ተገኝቷል ፡፡ | 11,111.51 |
| 5 | 17/02/09 | BPV | 526013 | 6116 | ዩኒቨርሲቲው ሪፈራል ሆስፒታል school of Medical Department of surgery neurosurgery unit አገልግሎት ለሰጡበት ብር 30,057 ከተከፈለው ገንዘብ ላይ መቆረጥ ያለበት የገቢ ግብር (30,057*35%ብር 10519.95መቆረጥ ሲገባው ለሁለት ፐርሰንት 601.14 | **9,918.81** |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | በልዩነት ብር9,918.81ሳይቆረጥ ተገኝቷል ። | |
| ድምር | | | | | | 51,654.73 |

አባሪ 5 ለተማሪዎች መማክርት እና ለሌሎች የስራ ክፍሎች የተከፈለ የማበረታቻ ክፍያ

| ተ.ቁ | ቀን | ደረሰኝ | የደረሰኝ ቁጥር | መደብ | የተከፈለበት ምክኒያት | የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 27/11/08 | JV | 577376 | 6116 | ሀምሌ ወር ለተማሪዎች መማክርት ከ200 ለ20 ተማሪወች 200 በማስብ ብር ለ20 ተማሪወች ብር 4000፣ ቶፕ አፕ በሚል 450 እሰከ 350 ለ6 ሰዎች ብር 2100 ቶፕ አፕ አይ.አር ኮሚቴናሌሎች ፣ ቶፕ አፕ አናላቲካል ፣ቶፕ አፕ ዳታ አናላቲካል እና አሲስታንስ ኢስትውደንት የተፈከለ | 11,900.00 |
| 2 | 30/12/08 | JV | 577378 | 6116 | የነሐሴ ወር ለተማሪዎች መማክርት ከ200 ለ20 ተማሪወች 200 በማስብ ብር ለ20 ተማሪወች ብር 4000፣ ቶፕ አፕ በሚል 450 እሰከ 350 ለ ሰዎች ብር 2100 ቶፕ አፕ አይ.አር ኮሚቴናሌሎች ፣ ቶፕ አፕ አናላቲካል ፣ቶፕ አፕ ዳታ አናላቲካል እና አሲስታንስ ኢስትውደንት የተፈከለ | 12,500.00 |
| 3 | 23/03/08 | JV | 578455 | 6116 | ህዳር ወር ለተማሪዎች መማክርት ከ200 ለ20 ተማሪወች 200 በማስብ ብር ለ20 ተማሪወች ብር 4000፣ ቶፕ አፕ በሚል 850 ብር 2100 ቶፕ አፕ አይ.አር ኮሚቴ 3300 ፣ቶፕ አፕ ዳታ አናላቲካል 2400 አሲስታንስ ኢስትውደንት 200 የተፈከለ | 10,750.00 |
| 4 | 21/08/09 | JV | 578821 | 6116 | የመጋቢት ካሽ እንደሚኒቲ 400 ለተማሪዎች መማክርት ከ200 ለ20 ተማሪወች 200 በማስብ ብር ለ20 ተማሪወች ብር 4000፣ ቶፕ አፕ በሚል 300 ቶፕ አፕ አይ.አር ኮሚቴናሌሎች 3000 ፣ ቶፕ አፕ አናላቲካል 3600 ፣ቶፕ አፕ ዳታ አናላቲካል እና አሲስታንስ ኢስትውደንት 400 የተፈከለ | 11,400.00 |
| 5 | 25/04/09 | JV | 5786467 | 6116 | የታህሳስ ወር ካሽ እንደሚኒቲ 400 ለተማሪዎች መማክርት ከ200 ለ20 ተማሪወች 200 በማስብ ብር ለ20 ተማሪወች ብር 4000፣ ቶፕ አፕ በሚል 850 ቶፕ አፕ አይ.አር ኮሚቴናሌሎች 3300 ፣ ቶፕ አፕ ዳታ አናላቲካል 3600እና አሲስታንስ ኢስትውደንት 200 የተፈከለ | 12,350.00 |
| 6 | 28/02/09 | JV | 578056 | 6116 | ጥቅምትወር ካሽ እንደሚኒቲ 400 ለተማሪዎች መማክርት ከ200 ለ20 ተማሪወች 200 በማስብ ብር ለ20 ተማሪወች ብር 4000፣ ቶፕ አፕ በሚል 850 ቶፕ አፕ አይ.አር ኮሚቴናሌሎች 3300 ፣ ቶፕ አፕ ዳታ አናላቲካል 2400እና አሲስታንስ ኢስትውደንት 200 የተፈከለ | 11,150.00 |
| 7 | 15/06/09 | JV | 578492 | 6116 | የታህሳስ ወር ካሽ እንደሚኒቲ 400 ለተማሪዎች መማክርት ከ200 ለ20 ተማሪወች 200 በማስብ ብር ለ20 ተማሪወች ብር 4000፣ ቶፕ አፕ በሚል 300 ቶፕ አፕ አይ.አር ኮሚቴናሌሎች 3300 ፣ ቶፕ አፕ ዳታ አናላቲካል 3600እና አሲስታንስ ኢስትውደንት 200 የተፈከለ | 11,600.00 |
| 8 | 30/08/09 | JV | 578839 | 6116 | የሚያዚያ ወር ለተማሪዎች መማክርት ከ200 ለ20 ተማሪወች 200 በማስብ ብር ለ20 ተማሪወች ብር 4000፣ ቶፕ አፕ በሚል 300 ቶፕ አፕ አይ.አር ኮሚቴናሌሎች 3300 ፣ ቶፕ አፕ ዳታ አናላቲካል 3600እና አሲስታንስ ኢስትውደንት 200 የተፈከለ | 11,400.00 |
| 9 | 01/07/09 | JV | 578499 | 6116 | የካቲት ወር ካሽ እንደሚኒቲ 400 ለተማሪዎች መማክርት ከ200 ለ20 ተማሪወች 200 በማስብ ብር ለ20 ተማሪወች ብር 4000፣ ቶፕ አፕ በሚል 300 ቶፕ አፕ አይ.አር ኮሚቴናሌሎች 3300 ፣ ቶፕ አፕ ዳታ አናላቲካል 3600እና አሲስታንስ ኢስትውደንት 200 የተፈከለ | 11,800.00 |
| | | | | | **ድምር** | **104,850.00** |

አባሪ 6 በሌክቸር አወር መከፈል ሲገባው በሰዓት በመከፈሉ በላይ በብልጫ

የተከፈለ እና የሂሳቡን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ የመምህራን

**<u>የትርፍ ሰዓት  ክፍያ ፤</u>**

| ተ.ቁ | ቀን | የደረሰኝ አይነት | የደረሰኝ ቁጥር | የሂሳብ መደብ | የተከፈለበት ምክኒያት | በብልጫ የተከፈለ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 30/05/09 | BPV | 578039 | 6116 | ዩኒቨርሲቲው በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ  ተማሪዎችን ላስተማሩ  መምህራን  ክጫና በላይ/over lode payment/ የመስከረም ወር  ለአንድ መምህር ላስተማሩበት(  86 ሰዓት የስተማረበት*በብር120 ብር10,320.0 በማስብ 2 መምህራን ብር20,640.00 እንዲሆን 81ሰዓት*120 ላስተማረ አንድ መምህራነብር9757፤ለሁለትመምህራን 48.44ሰዓት*65 *2መምህራነ ብር6297.2 ፤48.44ሰዓት*100 *ለ2መምህራንብር9688.00 **በድምር 46,382.2** የተከፈለ ሲሆን በመመሪያው መሰረት (86ሰዓት/ለ3ሰዓት= 28.67 ክሬዲት ሃወር*በብር120ብር3,440*2መምህራን **ብር6,880** +81/3*120 **ብር3,252.52**+48.44/3*65 ብር1049.53*2 **ብር2,099.06**+44.48/3*100 ብር1615*2 **ብር3,230**) በድምር **ብር15,461.58** መከፈል ሲገባው **ብር 46,382.20 የተከፍለ ሲሆን በልዩኒት ብር30195.48 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል** | **30195.48** |
| 2 | 30/05/09 | BPV | 578042 | 6116 | በዩኒቨርሲቲው በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ  ተማሪዎችን ላስተማሩ  መምህራን  ክጫና በላይ/over lode payment/ የመስከረም ወር  ለአንድ መምህር ላስተማሩበት(  86 ሰዓት የስተማረበት*በብር120 ብር10,320.0 በማስብ 2 መምህራን ብር20,640.00 እንዲሆን 81ሰዓት*120 ላስተማረ አንድ መምህራነብር9757፤ለሁለትመምህራን 48.44ሰዓት*65 *2መምህራነ ብር6297.2 ፤48.44ሰዓት*100 *ለ2መምህራንብር9688.00 **በድምር 46,382.2** የተከፈለ ሲሆን በመመሪያው መሰረት (86ሰዓት/ለ3ሰዓት= 28.67 ክሬዲት ሃወር*በብር120ብር3,440*2መምህራን **ብር6,880** +81/3*120 **ብር3,252.52**+48.44/3*65 ብር1049.53*2 **ብር2,099.06**+44.48/3*100 ብር1615*2 **ብር3,230**) በድምር **ብር15,461.58** መከፈል ሲገባው **ብር 46,382.20 የተከፍለ ሲሆን በልዩኒት ብር30195.48 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል** | **30195.48** |
| 3 | 25/12/08 | BPV | 68241 | 6116 | በቀን 25/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 68241 በሂሳብ መደብ 6116  በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከነሃሴ 1-30/2008 ገስት ሌክቸረሮች ትሬኒንግ ለሰጡበት (333.3333 ሰዓት ትሬኒንግ የሰጡበት* በሰዓት 120) በማሰብ  ብር 40,000  የተከፈለ ሲሆን ነገር ግን በመንግስት መመርያ መሰረት መከፈል የነበረበት (ሰዓት 333.3333/ ለ3 =111.1111 ክሬዲት ሃወር *በብር 120=  ብር 13,333.33 መከፈል ሲገባዉ በልዩነት (40,000 — 13,333.33) ብር **26,666.66** ከደንብና መመርያ ዉጪ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ | **26,666.66** |
| 4 | 16/12/08 | BPV | 68232 | 6116 | በቀን 16/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 68232 በሂሳብ መደብ 6116 በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ 13/11/08- 13/12/08 ዓ.ም ገስት ሌክቸረሮች ትሬኒንግ ለሰጡበት (292 ሰዓት ያሰለጠኑበት* በሰዓት 120) በማሰብ ብር 35,040 የተከፈለ ሲሆን ነገር ግን በመንግስት መመርያ መሰረት መከፈል የነበረበት (ሰዓት 292/ለ3= 97.33 ክሬዲት ሃወር *በብር 120 =ብር 11,680) መከፈል ሲገባዉ በልዩነት (35,040 — 11,680) ብር **23,360** ከደንብና መመርያ ዉጪ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ | **23,360** |
| 5 | 10/12/08 | BPV | 68230 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ 5/11/08- 5/12/08 ገስት ሌክቸረሮች ትሬኒንግ ለሰጡበት (224 ሰዓት ያሰለጠኑበት *በሰዓት ብር 120) በማሰብ ብር 26,880 የተከፈለ ሲሆን ነገር ግን በመንግስት መመርያ መሰረት መከፈል የነበረበት (ሰዓት 224/ለ3= 74.66 ክሬዲት ሃወር *በብር 120 )=ብር 8,960 መከፈል ሲገባ በልዩነት ( 26,880-8,960) ብር 17,920 ከደንብና መመርያ ዉጪ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ | ብር 17,920.00 |
| 6 | 5/12/08 | BPV | 68227 | 6116 | በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ 02/11/08 — 02/12/08 ገስት ሌክቸረሮች ትሬኒንግ ለሰጡበት (292 ሰዓት ያሰለጠኑበት *በሰዓት ብር 120 ) በማሰብ ብር 35,040 የተከፈለ ሲሆን ነገር ግን በመንግስት መመርያ መሰረት መከፈል የነበረበት (ሰዓት 292/ለ3 = 97.33 ክሬዲት ሃወር *በብር 120) =ብር 11,680  መከፈል ሲገባ በልዩነት (35,040- 11,680) ብር **23,360** ከደንብና መመርያ ዉጪ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ | ብር **23,360.00** |
| 7 | 5/12/08 | BPV | 68226 | 6116 | በቀን 5/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 68226 በሂሳብ መደብ 6116 በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ  ከ July2-2008  ገስት ሌክቸረሮች ትሬኒንግ ለሰጡበት (292 ሰዓት ያሰለጠኑበት *በሰዓት ብር 120) በማሰብ ብር 35,040 የተከፈለ ሲሆን ነገር ግን በመንግስት ደንብና መመርያ መሰረት መከፈል የነበረበት ( ሰዓት 292/ለ3= 97.33 ክሬዲት ሃወር *በብር 120) =ብር 11,680 መከፈል ሲገባዉ በልዩነት (35,040- 11,680) ብር 23,360 ከደንብና መመርያ ዉጪ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ | ብር 23,360.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | 02/12/08 | BPV | 68222 | 6116 | በቀን 2/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 68222 በሂሳብ መደብ 6116 በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ 5/10/08- 5/11/08) ገስት ሌክቸረሮች ትሬኒንግ የሰጡበት በሚል (224 ሰዓት ያሰለጠኑበት *በሰዓት ብር 120) በማሰብ ብር 26,880 የተከፈለ ሲሆን ነገር ግን በመንግስት ደንብና መመርያ መሰረት መከፈል የነበረበት (ሰዓት 224/ለ3 =74.66ክሬዲት ሃወር *በብር 120) ብር 8,960 መከፈል ሲገባዉ በልዩነት (26,880- 8,960) **ብር 17,920** ከደንብና መመርያ ዉጪ ተከፍሎ ተገኝቷል። | **ብር 17,920** |
